መግቢያ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 እና መ/ቤቱን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2003 እና 267/2011 መሠረት በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለመደበኛ ተግባራትና ለካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን፤ የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው ሕግ፣ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑን፣ ከምዝበራና ብክነት መጠበቁን ለማረጋገጥ የክልሉን የቆዳ ስፋት፣ የአወቃቀር እርከንና የሴክተር አደረጃጀት፣ለየመ/ቤቱ እንዲሁም ለመ/ቤታችን የተመደበውን በጀት፣ ያለውን የሰው ኃይል እና ሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመከተል ያከናወናቸውን ተግባራት ያካተተ አጠቃላይ ዘገባ በዚህ ጥራዝ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የተጠቃለለው ውጤት እንደሚያመለክተው፡-

1. መ/ቤቱ ከጥር 1/2014 እስከ ግንቦት 30/2015 ዓ/ም ባሉት ወራት የ360 መ/ቤቶችን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ337 (63.61%) መ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኗል፡፡ የሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት ውጤት በዚህ ሪፖርት ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡
2. የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 134(40%)፣በዞን 9(3%)፤በከተማ አስተዳደሮች 86(25%) ቀሪዎች 108(32%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሽፋን በእስትራቴጅካዊ ዘመኑ ቅድሚያ እንዲያገኙ ከተለዩት 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 43.42% የደረሰ ሲሆን የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ ደግሞ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የበጀት ሽፋን ብር 37,406,252,006.00 በመሆኑ ለ2014 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው በጀት ብር 80,104,669,397.00 አኳያ ሲታይ 47% ሲሆን ከገቢ በጀት አንፃር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የገቢ በጀት ብር 5,821,708,771.00 በመሆኑ በ2014 በጀት ዓመት ክልሉ በራሱ አቅም ለመሰብሰብ ከአቀደው የገቢ በጀት ብር 34,180,538,000.00 አኳያ ሲታይ 17% የኦዲት ሽፋኑ መድረሱን ያሳያል፡፡
3. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሰራተኞች እና ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገን የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል::
4. የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሥሩበትን ዝርዝር ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው::

5. የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች ከጥሬ ገንዘብ፣ከገቢ፣ከተሰብሳቢ፣ከወጪ፣ከተከፋይ፣ከሂሣብ ሪፖርቶችና ከንብረት አስተዳደር ኦዲት የተገኙ ሲሆኑ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 48,224,851.87 የገንዘብና ንብረት ጉድለት፣ማጭበርበር የተከሰተ እና ለግል ጥቅም የዋለ ሲሆን መ/ቤቶችም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- ሰሜን ሜጫ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 15,345,719.50 ፣አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 13,565,113.45 ፣አድማስ የገበሬዎች ህብረት ስራ መህበር ዩንዩን ብር 6,081,703.35 ፣ሰሜን ሜጫ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 3,891,720.56፣አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ልዩ ሐይል ም/ዘርፍ የጣና ክፍለ ጦር ብር 2,964,683.50፣አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ብር 2,188,044.04፣ወረታ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ብር 896,230.41፣ቡሩ ሜዳ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 885,482.68 ፣
- ሊቦ ከምከም ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 463,139.20፣ጃዊ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር **285,278.58** ፣ጃዊ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 274,395.00 ፣አንዳቤት ወረዳ ጎኖ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 248,064.26 ፣ቡሬ ከተማ አስ//አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 161,500.00፣ቡሬ ከተማ አስ//አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 140,260.07 ፣ባህር ዳር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 128,410.97 ፣ አንዳቤት ወረዳ ጎኖ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 127,012.65 ፣ሐርቡ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት ብር 105,944.96፣አወበል ወረዳ ወጀል ከተማ መጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 63,373.38፣ደሴ ከተማ ገንዘብ መምሪያ ብር 59,912.76፣አገው ግምጃ ቤት መሪ ማዘጋጃ ብር 55,274.28፣ታች ጋይንት ወረዳ አርብ ገብያ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 54,473.22፣በእነብሳ ሳር ምድር ወረዳ ሰኞ ገበያ ታዳጊ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ብር 54,464.30፣እንሳሮ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ብር 42,850.00 ፣ሃገረ ማርያም ከሰም ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 40,554.13 ፣የቲርቲራ ጤና አጠባበቅ ጣቢያው ብር 22,296.00፣ላይ ጋይንት ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 21,574.53፣ አምበሳሜ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 17,100.00 ፣ፋግታ ለኮማ ወረዳ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር 12,860.16 እና ዋድላ ወረዳ እስሳት ሀብት ተጠሪ ጽ/ቤት ብር 12,456.30፣ ከ**10,000.00** እና በላይ ጉድለት/ማጭበርበር በመፈፀም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

6. በዚህ አጠቃላይ ዘገባ ለየመ/ቤቱ ከተላከው የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች ዝርዝር ተለቅመው የተጠቃለሉ ግኝቶች እንዲሁም ከ2010 እስከ 2014 ባሉት 5 ዓመታት በተከናወነ ኦዲትና በተዘጋጁት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት አዝማሚያውን ለማሳየት የዋና ዋና ግኝቶች አማካይ ውጤት በግራፍ ተደግፎ ቀርቧል፡፡ የዚህ ሪፖርት ዋና ዓላማ የክልሉ ምክር ቤት የበጀትና መንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶችን ግኝቶች በመገምገም የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደሩን አጠቃላይ ሁኔታዎች ለማሻሻል ለሚደረጉ ውሳኔዎች እንዲጠቀሙበትና ተጠያቂነትንም ለማጠናከር በማሰብ የቀረበ ነው፡፡

7. የሪፖርቱ አቀራረብ የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤት፣በኦዲት ሂደት ወቅት እርምጃ የተወሰደባቸው ግኝቶች፣ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ የክትትል ኦዲት፣ያለፉት አምስት ዓመታት አፈጻጸም አዝማሚያ ትንተና ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየት በቅደም ተከተል ከምዕራፍ 1-5 በማካተት ሲሆን ለሪፖርቱ ደጋፊ አባሪዎች -------ገጽ በሪፖርቱ መጨረሻ ተያይዘዋል፡፡

ምዕራፍ -አንድ

1. የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም፣

1.1. የኦዲት ሽፋን፣

1.1.1. የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣በዞን ከተማ እና ወረዳ ደረጃ፣

በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በያልል/ማዕከል፣ዞን፣ከተማ እና □ረ□ ደረጃ የተያዘው ዕቅድና አፈፃፀም በንጽጽር ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-1 የኦዲት ሽፋን በክልል/ማዕከል፣ወረዳ፣ከተማ እና ዞኖች ከ2013 ክንዉን ጋር በንፅፅር

ተ.ቁ	ዞናዊ ስርጭት	የ2013	የ2014		ንጽጽር	
		ክንውን ብዛት	ዕቅድ ብዛት	ክንውን ብዛት	ከዓመቱ ዕቅድ %	የ2014 ከ2013 ክንውን%
1	የያልል /ማዕከል / መ/ቤቶች	40	143	**134**	0.94	3.35
2	ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር	3	7	**7**	1.00	2.33
3	ምዕራብ ጎጃም	12	28	**26**	0.93	2.17
4	ምስራቅ ጎጃም	21	44	**41**	0.93	1.95
5	ማዕከላዊ ጎንደር	9	19	**18**	0.95	2.00
6	ሰሜን ጎንደር	6	7	**6**	0.86	1.00
7	ምዕራብ ጎንደር	2	7	**6**	0.86	3.00
8	ደቡብ ጎንደር	17	31	**29**	0.94	1.71
9	አዊ ብሔ/አስተዳደር	12	20	**19**	0.95	1.58
10	ሰሜን ወሎ	0	5	**5**	1.00	5.00
11	ደቡብ ወሎ	7	19	**18**	0.95	2.57
12	ሰሜን ሸዋ	8	26	**24**	0.92	3.00
13	ዋግኽምራ ብሔ/ አስተዳደር	1	2	**2**	1.00	2.00
14	ኦሮሞ ብሔ/አስተደደር	0	**2**	**2**	1.00	2.00
	ድምር	138	**360**	**337**	0.93	2.44

- የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ክንውን ካለፈው በጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር በ199 መ/ቤቶች የጨመረ ሲሆን የጨመረበት ምክንያት በክልሉ የመረጋጋት ሁኔታ በመኖሩ በእቅድ የተያዙ ስራዎችን መስራት በመቻሉ ነው፡፡

1.1.2. የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን፤

የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ክንውን በአወቃቀር እርከን ሲታይ እንደሚከተለው ነው፡፡:

ሠንፀረዥ-2 የኦዲት ሽፋን በአወቃቀር እርከን

ተ.ቁ	የአወቃቀር እርከን	2014 ሂሳብ ኦዲት ክንውን	
		በመ/ቤት ብዛት	ከጠቅላላዉ ክንዉን በ%
1.	ያልል/ማዕከል	134	40
2.	ዞን አስተዳደር	9	3
3.	ወረዳ አስተዳደር	108	32
4.	ከተማ አስተዳደር	86	25
ድምር		**337**	**100**

1.2. የኦዲት ስልት፡-

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ከጥር 1/2014 እስከ ግንቦት 30/2015 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 337 መ/ቤቶች ውስጥ 271(80.41%) በንሞና እንዲሁም 66(19.59%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማና ጥያቄ ቀርቦባቸው በየነጥቦቹ መነሻነት በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸዉ፡፡

የኦዲት ሥራውን በአብዛኛ□ በመደበኛው እና በንሞና የኦዲት ስልት ለማከናወን ታቅዶ 80.41% በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረገ ሲሆን የኦዲት ሥልቱ □ለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኘና በዝርዝር ኦዲት ተደርጎ ከሚገኘው ጥቅም ያላነሰ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ዘመናዊ፣ በተመጣጣኝ የሰው ሀይል እና ወጭ ስራውን ለማከናወን የሚያስችል በመሆኑ ጊዜና ገንዘብ ቆጣቢ ስለሆነ እና የኦዲት ዘዴው በሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ ስጋት ያለበትን አካባቢ ትኩረት ስለሚሰጥ አዋጭ በመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

የንሞና ኦዲት ስልትን አስመልክቶ ካለፈዉ በጀት ዓመት አፈፃፀም የዕቅድ ክንውን በንጽጽር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-3 የኦዲት ስልት፤

ተ.ቁ	የኦዲት ስልት	2013ሂሣብ		2014 ሂሣብ	
		ክንውን ብዛት	%	ክንውን	%
1	ንሞና	100	72	271	80.41
2	ልዩ ኦዲት	38	28	66	19.59
	ድምር	**138**	**100**	**337**	**100**

በንሞና የኦዲት ዘዴ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የ2014 ክንውን 271(80.41%) ከ2013 ክንውን 100 (72%) ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት 171(171%) የጨመረ ሲሆን የ2014 የልዩ ኦዲት ክንውን 66(19.59%) ከ2013 ክንውን 38(28.%) ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት 28(73.68%) የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከባለፈው በጀት ዓመት በተሻለ ሁኔታ የኦዲት ስራ ማከናወን በመቻሉ ነው፡፡

1.3. የኦዲት አስተያየቶች፣

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመደበኛ እና በልዩ ኦዲት ተደርጎ ወጪ የሆኑ ሪፖርቶች 337 ሲሆኑ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ጋር ተነፃፅሮ እንደሚከተለው በሰንጠረዡ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-4 የኦዲት አስተያየቶች፣

ተ.ቁ	የኦዲት አስተያየት	2013 ሂሣብ		2014 ሂሣብ	
		የመ/ቤት ብዛት	በ%	የመ/ቤት ብዛት	በ%
1.	አስተያየት መስጠት አለመቻል	1	1	3	0.89
2.	አጥጋቢ አይደለም	6	4	15	4.48
3.	ከዚህ በስተቀር	59	43	198	58.75
4.	ንፁህ	27	20	54	16
5.	አስተያየት ያልተሰጠው	7	4	1	0.29
6.	ልዩ ኦዲት	38	28	66	19.59
	ድምር	138	100	337	100

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 337 መ/ቤቶች ውስጥ ለ198 (58.75%) ከዚህ በስተቀር፣ 3(0.89%) አሰተተያየት መስጠት አለመቻል፣15(4.48) አጥጋቢ አይደለም፤ለ54(16%) ንፁህ አስተያየት፣1(0.29%) መ/ቤት ሰነዱ በሰሜኑ በነበረው ጦርነት ምክንያት በመውደሙ አስተያየት ያልተሰጠው በመሆኑ እና 66(19.59%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ስራ በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት መስጠት የማይጠበቅባቸው ናቸው፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2013 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር " **ንፁህ አስተያየት የሚለው**" ከ27 ወደ 54 መ/ቤት (በ100%) የጨመረ መሆኑን ያሳያል፤"ከዚህ በስተቀር" ከ59 **ወደ 198 መ/ቤት (235%)** የጨመረ መሆኑ በአብዛኛው መ/ቤቶች ጉልህ ከሆኑ ግኝቶች ያልወጡ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን "**አስተያየት**

መስጠት አለመቻል" **ከ1 ወደ 3-መ/ቤት** (በ200%) የጨመረ መሆኑ የኦዲት ማስረጃዎች አቅርቦት ገደብ መጨመሩን የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል " **አጥጋሚ አይደለም የሚለው" ከ6 ወደ 15 መ/ቤት** (በ150%) የጨመረ ሲሆን አሁንም በሀብት አስተዳደር ስርዓቱ እና በሪፖርት አቀራረብ ላይ ያሉ ጉልህ መዛባቶች እየተስተካከሉ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡ የሂሳብ አሰራሩ የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ ከ38 ወደ 66 መ/ቤት (በ73.68%) መጨመሩ ህብረተሰቡ ብልሹ አሰራሮችን የመታገል ልምዱ እና መ/ቤታችን ስጋተ ኦዲትን መሰረት አድርጎ የመፈፀም አቅም እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ በየተቋማቱ ብልሹ አሰራር እየጨመረ መምጣቱን ያመላክታል፡፡

የኦዲት አስተያየት መገለጫዎች፤

1. "**አጥጋቢ አስተያየት**"የሚሰጠው ጉልህና መሰረታዊ የሚባል ግኝትና የአሰራር ችግር ያልተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡
2. "**ከዚህ በስተቀር"** የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው የኦዲት ሪፖርቶች ከተወሰኑ ጉልህ ነገር ግን መሰረታዊ ያልሆኑ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች በስተቀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይባቸው ናቸው፡፡
3. **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግስት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡
4. **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚለው አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች ደግሞ መንግስት የመደበላቸውን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እንዳዋሉት የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበላቸው፣የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸው በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተገለጹት አስተያየቶች የሚሰጧቸው መ/ቤቶች ግኝቶቻቸውና የአሰራር ችግሮቻቸው ጉልህና መሰረታዊ የሆነባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ በሪፖርቶቹ የቀረቡ ችግሮች ጉልህና መሰረታዊ መሆናቸውን በመገንዘብ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.3.1 **"አስተያት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 337 መ/ቤቶች ውስጥ 3(0.89%) መንግስት የመደበውን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እንዳዋሉት የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረቡ፣የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸው በጣም የተዳከመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መ/ቤቶች እና ለአስተያዩቱ መነሻ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.3.1.1. **ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

- በሪፖርት እና በባንክ ሂሳብ መቆጣጠሪያ ሌጀር መካከል የታዩ ልዩነት ብር 1,654,135.45፣
- ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 140,684.55፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ 4 ጥራዝ የመደበኛ እና 70 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 77,502.45፣
- በንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት የሚሰበሰቡ ልዩ ልዩ ገቢዎችን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 41,186,145.72፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወራረደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,280,639.48፣
- አላግባብ የተከፈለ የጥገና ክፍያ ብር 4,539.00፣
- አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል፣የስልክ ክፍያና የስልጠና አበል ብር 232,498.50፣
- ከበጀት ዓመቱ ውጪ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 4,090.00፣
- የተሽከርካሪ ነዳጅ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻል፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 343,379.64፣
- ከበጀት በላይ የተፈፀመ ወጪ ብር 1,055,885.05፣
- ለእንስሳት ተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሳብ ሪፖርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ከተፈጥሮ ሚዛኑ ውጪ ሪፖርት የተደረገ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 233,417.33፣
- ከተፈጥሮ ሚዛኑ ውጪ ሪፖርት የተደረገ የተከፋይ ሂሳብ ብር 361,992.22፣
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻል፣

1.3.1.2. **እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የመደበኛ፣የስፖርት ምክር ቤት እና የእንስሳት ሃብት
 የገቢ ሂሳብ ብር 971,161.57፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,673,375.84፣
- ተቀጽላ ሌጀሩ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 6,144,744.54፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 24,742,713.34፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተሰራለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 35,022,692.97፣
- ከግዥ ስርዓት ውጭ የተፈፀመ የአገልግሎት ግዥ ብር 5,580,000.00፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 45,440.00፣
- ያላግባብ የተፈፀመ የመስተግዶ ወጪ ብር 51,227.20፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 22,301,420.89፣
- ተቀጽላ ሌጀሩ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተከፋይ ሂሳብ 2,782,568.12፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 4,603,393.63፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተሰራለት የተከፋይ ሂሳብ ብር13,323,624.27፣

1.3.1.3. **ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- በባንክ ክሬዲት አድቫይሱ ላይ ገቢው የተሰበሰበበት ደረሰኝ መ/ሂ1 ቁጥር ከ-እስከ ባለመጠቃቀሱ የእንስሳት ህክምና የገቢ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለኦዲት ስራ ተፈልገው ሊቀርቡ ያልቻሉ12 ጥራዝ የስፖርት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 68,940.00 እና 99 ጥራዝ የመናኸሪያ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሂሳብ ብር 40,010.00፣
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ብር 4,684.00፣
- ከደመወዝ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ገቢ ግብር ብር 3,060.00፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ ብር 31,087,744.21፣
- በተሰብቢ ሂሳብ ሪፖርት እና ተቀጽላ ሌጀር መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በመብለጥ ብር 273,950.05 እና በማነስ ብር 1,300,079.28፣
- በተቀጽላ ሌጀር ተመዝግቦ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,119,444.13፣
- አላግባብ የተከፈለ የስልጠና ውሎ አበል ብር 73,912.00፣
- በሚመለከተው አካል ያልፀደቀ ወጪ ብር 299,774.51፣
- ያለምንም ማስረጃ የተፈፀመ ክፍያ ብር 2,600.00፣
- ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 996,232.26፣
- ከስራ ስፍር ልኬት በላይ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 2,360.00፣
- የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ ብር 6,415,837.29፣
- በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት እና ተቀፅላ ሌጀር መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በመብለጥ ብር 690,553.35 እና በማነስ ብር 2,646,981.73፣
- በተቀጽላ ሌጀር ተመዝግቦ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተከፋይ ሂሳብ ብር 4,019,152.30፣
- የስፖርት ምክር ቤት እና የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

1.3.2. **"አጥጋቢ አይደለም" የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው**

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት 337 መ/ቤቶች ውስጥ 15(4.48%) መ/ቤት የሂሳብ አያያዝና የገንዘብ አስተዳደራቸው እንዲሁም የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መ/ቤቶች እና ለአስተያዩቱ መነሻ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.3.2.1. **አምባ ጊወርጊስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 9,171.99፣
- ተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተሰብሳቢ ሂሳብ በደቢት አምድ ብር 3,489,005.22፣ እና በክሬዲት አምድ ብር 36,388.70፣

- በወቅቱ ያልተሰበሰ/ያልተወገደ/የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 482,710.86፡
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ በደቢት አምድ ብር 15,678.30 እና በክሬዲት አምድ ብር 3,475,672.57፡
- ባልተሟላ ማስረጃ የተፈፀመ ክፍያ ብር 37,285.30፡
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 915,285.00፡
- ያለአግባብ የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ ብር 30,000.00፡
- ያለአግባብ ላልተሰራ ስራ የተከፈለ የማሽነሪ ኪራይ ብር 290.815.92፡
- በብልጫ የተመዘገበ ወጪ ብር 4,995.75፡
- ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 2,978,534.48፡
- በሂሳብ ሚዛን ሙከራ ላይ የተፈጥሮ ሂሳብ ሚዛኑን ሳይጠብቅ ሪፖርት ተደረገ የተጣራ ሃብት ብር 12,220,532.98 እና የወጪ ሂሳብ 1,800,000.00፡
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፡

1.3.2.2. **መተማ ወረዳ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የስፖርት ምክር ቤት እና የእንስሳት ክሊኒክ ገቢ መሰብሰቢ ደረሰኞች ብር 88,235.50፡
- ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የመደበኛ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች 21 ጥራዝ ከ12 ቅጠል ብር 104,866.58፡
- ያለማረጃ የተመዘገበ ከክልል የተላከ የድጎማ ሂሳብ ብር 93,464,094.12፡
- በዕድሜ ያልተተነተነ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 12,360,704.43፡
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,511,167.68፡
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 11,665,500.76፡
- ያለግልጽ ጨረታ የተፈፀመ ግዥ ብር 960,014.96፡
- ያለምንም ማስረጃ ተፈፀመ ክፍያ ብር 500,000.00፡
- ጥራታቸው በባለሙያ ሳይረጋገጥ ገቢ ለሆነ ዕቃ የተፈፀመ ክፍያ ብር 430,303.97፡
- በድጋሜ ተፈጸመ ውሎ አበልና ስልጠና አበል ብር 98,974.00፡
- ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ የፀደቀ ሂሳብ ብር 19,000.00፡
- ከታለመለት ዓላማ ውጪ የተፈጸመ ክፍያ ብር 6,205.00፡
- ከመመሪያ ውጪ የተፈፀመ ክፍያ ብር 8,000.00፡
- በቋሚ ሆነ በኮንትራት ላልተቀጠሩ አንድ ግለሰብ አለአግባብ የተፈፀመ ውሎ አበልና የነዳጅ ሂሳብ ብር 284,104.50፡
- አላግባብ የተፈጸመ ውሎ አበል ብር 17,139.00፡

- የነዳጅ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻል፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ ተከፋይ ሂሳብ ብር 47,666,475.36፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 40,616,913.73፣
- በሌጀርና እና በሪፖርት መካከል የታየ ልዩነት ዩኒሴኤፍ ሂሳብ ሪፖርት በማነስ ብር 18,377.50 እና በመብለጥ ብር 232,044.80፤ጅኩብ ሂሳብ ሪፖርት በመብለጥ ብር 540,000.00 እና ዋንዋሽ ሂሳብ ሪፖርት በማነስ ብር 164,445.04፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልተጠቀ የተጣራ ሀብት ብር 24,724,102.45፣
- በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የፀደቀ ሂሳብ ብር 800,000.00፣
- የስፖርት ምክር ቤት፣ የጤና ተራድኦ እና የአማራ ልማት ማህበር ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

1.3.2.3. **ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- በባንክ ክሬዲት አድቫይስ ላይ ገቢው የተሰበሰበበት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ በመሆኑ የመደበኛ፣የመናኸሪያ እና እንስሳት ጤና ሪቮልቪንግ ፈንድ ገቢ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ/ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 19,315,870.30፣
- ከግዥ መመሪያ ውጭ የተፈጸመ የቴክኖ እስፓርክ ግዥ ብር 5,500.00፣
- አላግባብ በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 40,211.00፣
- በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበልና የስልጠና አበል ብር 159,825.00፣
- የግንባታ ስራ ዝርዝር ሳይቀርብለት የተፈፀመ የመንገድ ግንባታ ክፍያ ብር 3,235,101.48፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ/ያልተወራረደ የተከፋይ ሂሳብ ብር 10,093,734.56፣
- የስፖርት ምክር ቤት እና የመናኸሪያ ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- ንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

1.3.2.4. **አነደድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ያልተሰበሰ ስራ ግብር ብር 12,332.88፣
- ከውል መዘግየት ያልተሰበሰ ገቢ ብር 2,183.43፣
- ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የመደኛ ገቢ ደረሰኞች ብር 15,500.00፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የመናኸሪያ ገቢ ሂሳብ ብር 57,029.00፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የእንስሳት ጤና የገቢ ሂሳብ ብር 320,980.33፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የስፖርት ምክር ቤትገቢ ሂሳብ ብር 192,900.00፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 28,016,251.24፣

- ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ ብር 34,600.00፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎአበልና ስልመና አበል ብር 186,020.15፣
- በወቅቱ ያልተወራደ የተከፋይ ሂሳብ ብር 32,139,081.17፣
- ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 4,043,008.64፣

1.3.2.5. **እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- በባንክ ማስታወቂያ እና በባንክ ሪፖርት ሚዛን መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በማነስ ብር 212,926.50፣
- በባንክ ማስታወቂያ እና በባንክ ሪፖርት ሚዛን መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በመብለጥ ብር 1,788.713.02፣
- የሂሳብ መቆጣጠሪያ ሌጀር ያልተዘጋጀለት በባንክ ያለ ገንዘብ ብር 9,256,281.58፣
- የሂሳብ መቆጣጠሪያ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተጣራ ሀብት ሂሳብ ብር 3,446,974.13፣
- ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 5,607.69፣
- አላግባብ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ብር 2,290,205.28፣
- ለኦዲት ስራ ተፈልጎ ያልቀረቡ 19.2 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 40,645.00፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የመደበኛ ገቢ ሂሳብ ብር 868,184.87፣
- የስፖርት ምክር ቤት የገቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ/ያልተወራረደ/ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 13,887,739.18፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 606,211.82፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 569,641.82፣
- ከሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 11,496,018.24፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ክፍያ ብር 8,044.00፣
- ባልተሟላ ማስረጃ የተፈጸመ ክፍያ ብር 2,388.16፣
- ከበጀት አመቱ ውጭ የተፈጸመ ክፍያ ብር 80,078.00፣
- በተሳሳተ የሂሳብ መደብ የተከፈለና የተመዘገበ ወጪ ብር 27,168.00፣
- ከመንግስት በጀት ለግላዊ ጉዳይ የተፈጸመ ክፍያ ብር 15,000.00፣
- የግንባታ ስራ የስፍር ልኬታ ወረቀት ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ ብር 834,378.62፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 18,832,945.08፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 128,233.05፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 382,951.39፣

- ከተፈጥሮ ሂሳብ ሚዛኑ ውጪ ሪፖርት የተደረገ የተከፋይ ሂሳብ ብር 89,494.40፣
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

1.3.2.6. **ምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ፈሰስ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 75,693.79፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ 34.62 ጥራዝ የስፖርት ም/ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 55,542.00፣
- በወቅቱ ሳይሰበሰብ /ሳይወራረድ/የተገኘ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 38,483,515.56፣
- አላግባብ የተከፈለ የስልጠና እና የውሎ አበል ሂሳብ ብር 488,152.60፣
- አላግባብ የተከፈለ የዶዘር ኪራይ ብር 2,268.65፣
- ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ ሂሳብ ብር 580,319.06፣
- ያለምንም ማስረጃ በወጪ ፀድቆ ክፍያ ተፈፅሞ የተገኘ ሂሳብ ብር 249,888.00፣
- ለኦዲት ስራ ተፈልጎ ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ሰነዶች ከስፖርት ምክር ቤት ብር 80,000.00 እና ከጤና ተራድኦ ብር 40,150.78 ፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ /ያልተወራረደ/ የተከፋይ ሂሳብ ብር 36,903,844.04፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 379,047.03፣
- በብልጫ የተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 27,032.26፣
- ከተፈጥሮ ሚዛኑ ውጪ ሪፖርት የተደረገ የተጣራ ሃብት ሂሳብ ብር 672,843.06፣
- የአልማ በጀት ማስፈጸሚያ፣የናይል ኢንሹራንስ፣የምዕተ ዓመቱ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ካፒታል በጀት፣የዋን ዋሽ፣የፋይናንስ ግልፀኝነት ፣የመንገድና ትራንስፖርት መናሀሪያ፣ የእንስሳት ጤና መድሃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሳብ የተሟላ ወርሀዊ ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣
- ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 5,125,717.09፣
- የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

1.3.2.7. **አብክመ ትምህርት ቢሮ**

- ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 4,002.68፣
- ከውለታ ውጪ የተፈፀመ ክፍያ ብር 354,970.00፣
- የስራ ስፍር ለረኬት ወረቀት ሳይዘጋጅለት የተከፈለ የግንባታ ወጪ ብር 491,749.62፣
- በባንክ ማስታወቂያ ሚዛን እና በባንክ ሪፖርት ሚዛን መካከል ያለ ልዩነት ባንክ ሪፖርት በመብለጥ ብር 968,375.40፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 49,086,244.17፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 21,941,522.97፣
- በሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 73,698.56፣

- በብልጫ የተከፈለ ወጪ ብር 463,110.76፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 83,869.00፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 23,828,843.94፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 12,357,275.38፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 53,953,230.25፣
- ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 2,645,635.67፣

1.3.2.8. **ሰሜን ሸዋ ነ/ፋ/ድ/ሰጭ/ማዕከል**

- በንክ ማስታረቂያ ከሪፖርት በመብለጥ የታየ ልዩነት ብር 5,826,546.88፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 9,729,978.42፣
- ከሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ 16,923,715.70፣
- ከደመወዝ እና ከጥቅማጥቅ ክፍያ ላይ በግብር አሰባሰብ መሰረት ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 498575.45፣
- ከግዥ ስርዓት ውጪ የተፈፀሙ የመኪና ጎማ እና የፈርኒቸር ግዥ ብር 2,306,499.54፣
- ደረሰኝ ያልቀረበለት የአልጋ አበል ብር 2,999.95፣
- አላግባብ የተከፈለ የአልጋ አበል ብር 6,000.00፣
- አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ ብር 369,776.50.፣
- ከበጀት አመቱ ውጪ የተከፈለ የትራንስፖርት እና ውሎ አበል ብር 5,910.00፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 8,515,709.24፣
- ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ ብር 180,859.63፣

1.3.2.9. **ስናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል**

- በባንክ ማስታረቂያ እና በሪፖር መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በማነስ ብር 153,222.06፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ገቢ ሂሳብ ብር 46,194.00፣
- ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ ቅጣት ገቢ ብር 22,888.94፣
- ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 3,159,028.78፣
- ከሶስተኛ ወገን ያለቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 3,138,581.53፣
- ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ገቢ ብር 46,194.25፣
- ከግዥ ስርዓት ውጪ የተፈፀመ ክፍያ ብር 882,120.51፣
- በተሳሳተ የሂሳብ መደብ የፀደቀ ወጪ ብር 16,988.00፣
- ባልተሟላ ማስረጃ የተከፈለ ክፍያ ብር 267,841.50፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና የጥራንስፖርት ሂሳብ ብር 57,158.07፣
- ከመመሪያ ውጭ የተሰጠና ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 259,734.92፣

- የስራ ዝርዝር ያልቀረበለት የውሃ ግንባታ ክፍያ ብር 53,911.06፣
- በኖርማላይዜሽን መሰረት ነዳጅ ባለ መቀዳቱ የነዳጅ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ የስፖርት ምክር ቤት ሂሳብ ብር 105,045.00፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 2,746,266.52፣
- ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 3,631,986.73፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 7,136,018.09፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጣራ ሀብት ብር 1,607,381.67፣

1.3.2.10. **ሸበል በረታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተቀነሰ ቅድመ ግብር ብር 445,925.87፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 26,336,056.64፣
- ከግዥ ስርዓት ውጪ የተፈፀመ ግዥ ብር 713,581.70፣
- አላግባብ የተፈፀመ የውሎ አበል እና የስልጠና አበል ብር 153,198.65፣
- የግንባታ የስራ ዝዝር ሳቀርብ የፈፀመ የውሃ ግንባታ ክፍያ ብር 12,870.00፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 13,619,183.31፣
- ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ሂሳብ ብር 12,060.00፣

1.3.2.11. እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል

- በባንክ ማስታረቂያ መግለጫ እና በሪፖርትና በሌጀር ከወጪ ቀሪ መካከል የታየ ልዩነት
- ሪፖርት በማነስ ብር 887,288.17፣
- ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 210,814.67፣
- ለኦዲት ያልቀረበ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ ሂሳብ ብር 433,080.00፣
- ለኦዲት ያልቀረበ የእስሳት ተዘዋዋሪ ገቢ ሂሳ ብር 9,741.33፣
- በወቅቱ ያልተወራረደ /ያልተሰበሰበ / ሂሳብ ብር 25,434,816.52፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለተ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 535,625.07፣
- ከሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 22,306,779.97፣
- የተሽከርካሪ ኖርማላይዜሽን ሳይጠቀሙ የተከፈለ የነዳጅ ሂሳብ ብር 1,701,920.42፣
- ባልተሟላ ማስረጃ የተፈፀመ ክፍያ ብር 21,877.50፣
- አለግባብ የተከፈለ የደንብ ግዥ ብር 264,632.00፣
- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 5,226.00፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 8,005,580.87፣
- የዕድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለተ የተከፋይ ሂሳብ ብር 138,258.11፣
- ስራላይ ያልዋለ በጀት ብር 298,551.98፣

- ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ ብር 228,852.58፣

1.3.2.12. **ጎዛምን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል**

- በባንክ ማስታወቂያ እና በባንክ ሪፖርት መካከል የታየ ልዩነት ሪፖርት በማነስ ብር 1,293,240.30፣
- ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ገቢ ብር 25,571.80፣
- ኦዲት ማድረግ ያልተቻለ የመናህሪያ ገቢ ሂሳብ ብር 63,889.00፣
- ለኦዲት ያልቀረበ 41.34 ጥራዝ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብር 103,350.00፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 18,362,263.12፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀለት የተሰብሰቢ ሂሳብ ብር 174,685.88፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 406,053.80፣
- ከ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 12,409,431.73፣
- ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደርሰኝ የተቆረጠለት ንብረት ብር 456,674.36፣
- ደረሰን ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 44,705.85፣
- ስርዝ ድልዝ በሆነ ማስረጃ የተፈፀመ ግዥ ብር 255,531.40፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 5,526.00፣
- የንብረት ገቢ ደረሰኝ እና ርክክብ ቬርባል ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ ብር 117,895.97፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 20,238,841.30፣
- የእድሜ ትንተና ያልተዘጋጀ የተከፋይ ሂሳብ ብር 175,741.84፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 164,895.14፣
- ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ ብር 582,859.26፣
- የንብረት ሂሳብን ማመዛዘን አለመቻሉ፣

1.3.2.12. **እናርጅ እናውጋ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- የእንስሳት ሃብት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለኦዲት ስራ ሊቀርቡ ያልቻሉ የስፖርት ምክር ቤት የገቢ ደረሰኞች ብር 257,140.00፣
- ለኦዲት ስራ ሊቀርቡ ያልቻሉ የመናህሪያ የገቢ ደረሰኞች ብር 43,510.00፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 27,367,214.32፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 14,458,486.59፣
- ከ3ኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,208,366.28፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር 13,391,106.92፣
- ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ ብር 380,493.51፣

- አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ብር 9,332.68፣
- የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ ብር 1,087,907.85፣

1.3.2.14. **ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል**

- ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሌጀር በማነስ ብር 871,339.65፣
- የመደበኛ፣የእንስሳት ጤና እና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 38,664.49፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 47,019,143.26፣
- ከሶስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልቀረበለት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 31,270,998.28፣
- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 4,510.01፣
- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 63,755.80፣
- ያለውለታ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ ብር 66,549.68፣
- በተሳሳተ ሂሳብ መደብ የተመዘገበ ወጪ ሂሳብ ብር 25,684.79፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረቡ የወጪ ሰነዶች ብር 318,231.01፣
- የስፖርት ምክር ቤት እና የእንስሳት ጤና ሂሳብ ወርሃዊ ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣
- ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ ብር 200,747.86፣

1.3.2.15. **ደሴ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት**

- ከሶስት ክፍለ ከተሞች መሂ 64 ሊቀርብ ባለመቻሉ በገንዘብ ያገኙ የተሰበሰበውን ገቢ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- በማነስ ተወስኖ ያልተሰበሰበ የንግድ ስራ ግብር ብር 15,582.94፣
- ተወስኖ ያልተሰበሰበ ፍሬ ግብርና ታክስ ብር 513,548.34፣
- ያልተወሰነና ያልሰበሰበ ግብር፣ታክስ እና አገልግሎት ክፍያ ብር 5,400.00፣
- ያልተሰበሰበ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ብር 28,659.54፣
- በክፍያ ውል ስምምነት መሰረት ያልተሰበሰበ ግብርና ታክስ 34,885.15፣
- የ20 የግብር ከፋይ ድርጅቶች የስራ ግብር ገቢ ማድረጋቸው የሚያሳይ ማስረጃ ባለመኖሩ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- የሂሳብ መዝገባቸው በታክስ ኦዲት ያልተመረመሩ በመሆኑ የግብር ከፋይ ፋይሎችን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ።
- የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻ፣
- የቴምብር ሽያጪ ሂሳብን ማመዘዘን አለመቻሉ፣
- የሊዝ ውል እና ሌሎች ማስረጃዎች የሌላቸው በመሆኑ የሊዝ ከፋዮችን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

- የውዝፍ ሂሳብን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- በእቅዱ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 490,660,624.86፣
- የሆጤ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ደረሰኝ ማመዛዘን አለመቻሉ፣

1.4. መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች፣

ይህ ሪፖርት እስከተጠቃለለበት ሰኔ 24/2015 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ክልል ማዕከል መ/ቤቶች

1. የአብክመ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን
2. ጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤት
3. ጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት 2013
4. ምዕራብ ደንቢያ ወረዳ ፍርድ ቤት
5. ደባርቅ ወረዳ ፍርድ ቤት
6. ሊቦከምከም ወረዳ ፍርድ ቤት
7. ሰሜን ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤቶች መምሪያ
8. አሳግርት ወረዳ ፍርድ
9. ሀገረ ማያም ከሰም ወረዳ ፍርድ ቤት
10. አንጎለላና ጠራ ወረዳ ፍርድ ቤት
11. ደብረ ብርሃን ጤና ሳይንስ ኮሌጅ
12. ደነባ ሆስፒታል
13. አንባሰል ወረዳ ፍርድ ቤት
14. ደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት
15. ቦረና ወረዳ ፍርድ ቤት
16. ደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት
17. ደብረ ታቦር ማረሚያ ቤት
18. ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት
19. ደብረ ታቦር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ
20. ሸበል በረታ ወረዳ ፍርድ ቤት
21. ደብረ ኤሊያስ ወረዳ ፍርድ ቤት
22. ደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል
23. ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት
24. ባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት

ባህርዳር ከተማ አስተዳደር

25. ፋሲሎ ክፍለ ከተማ ባህር ዳር ጤና ጣቢያ

ምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር

26. ሰሜን አቸፈር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል
27. ፍኖተ ሰላም ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር

28. **ደብረ ማርቆስ ከተማ/አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት**
29. **ደባይ ጥራት ግን ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት**
30. **እነማይ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት**
31. **ደብረ ኤሊያስ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት**
32. **አዋበል ወረዳ** ነ/ፋ/ድ/ማዕከል
33. **ምስራቅ ጎጃም ዞን** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
34. **ሸበል በረታ ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
35. **እነማይ ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
36. **ጎዛም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት**
37. **ጎንቻ ሲሶ እነብሴ ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
38. **ደብረ ኤልያስ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
39. **ባሶ ሊበን ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
40. **አነደድ ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
41. **ቢቡኝ ወረዳ** ነ/ፈ/ድ/ማዕከል
42. **አማኑኤል ጤና አጠባበቅ ጣቢያ**

ማዕከላዊ ጎንደር ዞን አስተዳደር

43. ጎንደር ገብሬል ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር

44.ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል

45.ዳባት ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ማዕከል

46.ደባርቅ ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ምዕራብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

47.መተማ የሐንስ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር

48.ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ማዕከል

49.ደቡብ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

50.ታች ጋይት ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ማዕከል

51.አስቴ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

52.ደብረ ታቦር ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር

53.ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማ

54.ጓንጓ ወረዳ ነ/ፍ/ድ/ማዕከል

55.ጃዊ ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ማዕከል

56.አካሻ ጓጉሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

57.ዳግላ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

58.ማሻ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

59.ልጓማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

60.ቅዳሜ ገበያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

61.ደሴ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

62.ደሴ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት

63.ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከ

ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር

64.ጠባሴ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

65.ደብረ ብርሃን ሀይለ ማሪያም ማሞ ከ/ት/መሰናዶ ት/ቤት

66.አረርቲ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ

67.ሞረትና ጅሩ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት

68.ሚዳ ወረሞ ገቢዎች ጽ/ቤት

69.ሚዳ ኦረሞ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

70.አለም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

71.ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል

በአጠቃላይ መልስ አሰጣጡ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛ ኦዲት ከተደረገ 100 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 30(30%) ጋር ሲነጻጸር በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 271 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 71(26.19%) ስለሆኑ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እየቀነሰ የመጣ ሲሆን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት ሥርዓት ከማጠናከር አኳያ ድክመቶች እንዳሉ የሚያመላክት እና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ በኩል እጥረቶች እንዳሉባቸው ያሳያል፡፡ በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 66 መ/ቤቶች ውስጥ ደግሞ እርምጃ ያልተወሰደባቸው 66መ/ቤቶች(100%) በመሆናቸው እርምጃ የመውሰድ ሂደቱ ችግር ያለበት መሆኑን ይሳያል፡፡

1.5 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፣

1.5.1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለት፣

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየጊዜው ቁጥጥር እያደረጉ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዋና ኦዲተር መ/ቤት በኩል የበጀት ዓመቱን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማረጋገጥ ስራ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ያለ ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የኦዲት ሥራዎች ላይ ሁኔታዎች ትኩረት ሲስቡና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲረጋገጥ በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በወቅቱ በመቀበል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የማመዛዘን ተግባር የሚከናወን ሲሆን የኦዲት ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-5 **የጥሬ ገንዘብ ጉድለት**

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች	ጉድለት				የገንዘብ ያዥ ብልጫ		የሌጀር ከወጪ ቀሪ ከቆጠራ ልዩነት			
		የመ/ቤት ብዛት	ከአሁን ገንዘብ ያዥ	የመ/ቤት ብዛት	ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ	የመ/ቤት ብዛት	የገ/መጠን	የመ/ቤት ብዛት	በመብለጥ	የመ/ቤት ብዛት	በማነስ
1.	ክልል/ማዕከል							1	52,962.50		
2.	ባህር ዳር ከተማ					1	3,827.07				
3.	ምዕ/ጎጃም	1			3,891,720.56	1	109,288.73				
4.	ምስራቅ ጎጃም	2			117,837.68	1	109,341.00	1	67,577.18		
5.	ማዕከላዊ ጎንደር									1	2,596,842.49
6.	ሰሜን ጎንደር										
7.	ምዕራብ ጎንደር										
8.	ደቡብ ጎንደር	1	21,574.53	3	1,413,842.83			1	72,267.46		
9.	የአዊ ብሔ/አስተ/	2			68,134.44						
10.	ሰሜን ወሎ	2			128,240.96						
11.	ደቡብ ወሎ							1	871,339.65		
12.	ሰሜን ሸዋ	2			6,185.63						
13.	ኦሮሞ ብሔ/አስተ/										
14.	ዋግኽምራ ብሔ/አ										
ድምር		10	21,574.53	3	5,625,962.10	3	222,456.80	4	1,064,146.79	1	2,596,842.49

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,647,536.63 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,625,962.10 ከቀድሞ ገንዘብ ያዦች የተገኘ ጉድለት ነው፡፡

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ/30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ4 መ/ቤቶች ብር 1,064,146.79 የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ እና በ1 መ/ቤት የተቆጠረ ገንዘብ ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ ብር 2,596,842.49 ተስተውሏል፡፡ ዝርዝሩን (አባሪ 2 ይመልከቱ፡፡)

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየባቸው መ/ቤቶች፡-

- ሰሜን ሜጫ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ከሰኔ 27/2010 አስከ ነሀሴ /2014 ዓ/ም፣ ከየካትት 21/2006 ዓ.ም እስከ ነሀሴ/ 2014 ዓ/ም እና ከየካትት 21/2006 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 2014 ዓ/ም የሰበሰቡት ገቢ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 3,891,720.56፣
- ወረታ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት የጽ/ቤቱ ዋና ገንዘብ ያዥ የሆኑት ከ01/10/2013 እስከ 30/12/2013 ያቀሳቀሱት የገቢ እና ወጪ ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 896,230.41፣
- ሊቦ ከምከም ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩ ስራ ከጀመሩበት ከየካቲት 28/2006 እስከ ሰኔ 30/2007 ዓ/ም ያቀሳቀሱት የጥሬ ግንዘብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 463,139.20፣
- ሐርቡ ከተማ መሪ ማዘጋጃ የቀድሞው ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ12/6/2006 እስከ 30/10/2010 ዓ/ም ያቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እና አንድ ግለሰብ ገንዘብ ያዥ ሆነው በትብብር በሰሩብበት ጊዜ ውስጥ ያከናወኑት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት በድምሩ ብር 105,944.96፣
- አወበል ወረዳ ወጀል ከተማ መጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ እና ንብረት ክፍል ሰራተኛ በመሆን ከ21/02/2009 አስከ 15/5/2012 ዓም ድረስ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሰበሰቡት ገንዘብ እና ስራ ላይ ያወሉት ፣ዋና ገንዘብ ያዥ ሰራተኛ በመሆን ከ21/11/2013 አስከ 30/10/2014 ዓም ድረስ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሰበሰቡት ገንዘብ እና ስራ ላይ ያወሉት ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ በጉድለት የተገኘ 63,373.38፣
- አገው ግምጃ ቤት መሪ ማዘጋጃ ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ22/11/2011 ዓ/ም አስከ 20/8/2014 ዓ/ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 55,274.28፣
- ታች ጋይንት ወረዳ አርብ ገብያ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ዋና ገንዘብ ያዥ የሆነት ከጥር 1/2010 መስከረም 28 /2012 ዓም ድረስ ከመደበኛ እና ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የሰበሰቡት እንዲሁም የፈጸሙት ወጪ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 54,473.22፣

- በእነብሳ ሳር ምድር ወረዳ ሰኞ ገበያ ታዳጊ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ11/1/2010 አስከ 7/12/2012 በሞ/ 64 የሰበሰቡት ገቢና በወጪ ማስመስከሪያ ወይም መሂ/7 ወጪ የፈፀሙበት ሲመዛዘን የተገኘ ጉድለት ብር 54,464.30፣
- የቲርቲራ ጤና አጠባበቅ ጣቢያው ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ12/12/2008 እስከ 17/09/2009 ዓ/ም ያቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 22,296.00፣
- ላይ ጋይንት ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት በስማቸው በተሰብሰቢ የተያዘ ከ2011 ወደ 2012 የዞረ እና 1/11/2011 አስከ 24/02/2013 ዓ/ም ከባንክ በቸክ ያወጡትና ለተለያዩ ተግባራት ከ1/11/2011እስከ 24/2/2013 ለተለያዩ ተግባራት ያወጡት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ በጉድለት ብር 21,574.53፣
- ፋግታ ለኮማ ወረዳ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከ25/1/2010 እስከ 2/4/1011 ዓ.ም ያቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 12,860.16፣
- አንጎለላና ጠራ ወረዳ ሰርቲ የመ/ደ/ትቤት የነበሩት ከ23/10/2008 እስከ 16/5/2010 ያቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 4,034.00፣
- ጫጫ ወረዳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ገንዘብ ያዥ የነበሩት ከመጋቢት 23/2008 እስከ ነሐሴ 11/2011 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,151.63፣

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጋር በተያያዘ ለግኝቶች በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት፤

- በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ ከተያዘው የሌጀር ከወጪ ቀሪ ሚዛን ጋር እንዲመሳከር አለማድረግ፣
- የተቋማት የሂሳብ አያያዝ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆኑ፣
- ገንዘብ ያዦች የስራ ለውጥ በሚያደርጉበት ጊዜ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ በውስጥ ኦዲተር እየተመረመረ ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፣
- በረዳት ገንዘብ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ በየእለቱ ለዋና ገንዘብ ያዦች ፈሰስ አለማድረግ፣
- የግዥ ሰራተኞች በተሰብሳቢ ሂሳብ የወሰዱትን ገንዘብ በወቅቱ ሳያወራርዱ በድጋሜ ጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ በመሆኑ በቆይታ ብዛት የጥሬ ገንዘብ ብክነት የሚከሰት መሆኑ፣

በመሆኑም ከገንዘብ ያዦች እና ከእቃ ግዥ ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ለፍትህ አካላት ብናሳስብም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

1.6. የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

1.6.1. የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት *የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 15,526,533.70 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ሰሜን ሜጫ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 15,345,719.50 የፅለት ገንዘብ ሰብሳቢ የነበሩት 3-ሰራተኞች ከንብረት ክፍል ወጪ አድርገው ገንዘብ የሰበሰቡበትን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በመሰወር በእነዚህ ደረሰኞች የተሰበሰበን ገቢ ለግል ጥቅም በማዋላቸው በጠፉ ደረሰኞች ገንዘብ ማስመለሻ መመሪያ መሰረት ሲሰላ ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የገቢ ሂሳብ፣በበራሪው እና በቀሪው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቅጠል የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በማለያየት በበራሪው የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በቀሪው የገቢ ደረሰኝ ቅጠል ዝቅ አድርጎ በማስፈር በ4-የፅለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ለግል ጥቅም የዋለ የገቢ ሂሳብ፣ 4-የእለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ከመ/ቤቱ እውቅና ውጭ በህገ-ወጥ መንገድ በራሳቸው ጊዜ ህገ-ወጥ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በማሳተም ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የገቢ ሂሳብ ፣
- ቡሬ ከተማ አስ//አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 140,260.07 በ02 ቀበሌ ለተከናወነው የኮብል እስቶን ንጣፍ የአፈር ቁፋሮ እና የ03 ጠጠር ለተሰራው ስራ ክፍያ ሲፈፀም የቫት ደረሰኝ ሳይቆረጥ በህገ-ወጥ ደረሰኝ የተሰበሰበ እና ለግለሰብ ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- ሃገረ ማርያም ከሰም ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 40,554.13 የወረዳው ገንዘብ ጽ/ቤት የመኪና ጥገና ሲያከናውን ጋራዥ ቤቱ የተጨማሪ እሴት ተመዝጋቢ ሆኖ እያለ ህገ-ወጥ ደረሰኝ በማቅረብ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ብናሳስብም እስከ ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

1.6.2. ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,398,051.18

የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ እቃ/አገልግሎት ሲያቀርብ ለክፍያው የቫት ደረሰኝ/ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት እና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃው እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ1 መ/ቤት ብር 2,398,051.18 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክሱ ለመንግስት ገቢ ሳይደረግ ክፍያ የተፈፀመበት መ/ቤት፡-

- መተማ ዩሀንስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,398,051.18 በቤቶች ልማት ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት የኮንቴነር ቤት ግንባታ፣የዲች ቦይ እና የስላብ ካልበርት ግንባታ ተከናውኖ ለጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ሽርክና ማህበራት ክፍያ ሲፈፀም ለመንግስት ገቢ ያልሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ አቅራቢው ታክሱን ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርጎ ማስረጃ እንዲያቀርብ መደረግ እንዳለበት እያስገነዘብን ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ በመመስረት የተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

1.6.3. ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 337 መ/ቤቶችውስጥ በ68/20.17%/ መ/ቤቶች ብር 412,805,098.78 ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት ገቢው በ□ቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ □ር□ሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-6 በውዝፍ የሚገኝ ገቢ፣

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የ2013 በውዝፍ የሚገኝ/ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ			የ2014 በውዝፍ የሚገኝ /ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	2	194,555.06	0.03	22	2,001,738.41	0.48
2	ባህር ዳር ከተማ	1	425,658,470.67	74.73	1	218,912,512.60	53.03
3	ምዕራብ ጎጃም	2	303,355.67	0.05	4	968,927.49	0.23
4	ምሥራቅ ጎጃም	9	19,144,716.37	3.36	20	44,436,278.05	10.76
5	ማዕከላዊ ጎንደር	1	118,203,059.47	20.75	3	129,701,242.19	31.42
6	ሰሜን ጎንደር	2	181,753.01	0.03	1	140,684.55	0.03
7	ምዕራብ ጎንደር	1	40,154.98	0.01			0
8	ደቡብ ጎንደር	3	856,921.27	0.15	2	9,358,793.27	2.27
9	አዊ ብሔረሰብ	1	46,826.16	0.01	6	2,630,526.88	0.64
10	ደቡብ ወሎ	1	1,865,830.66	0.34	5	1,710,753.70	0.41
11	ሰሜን ወሎ				0	0	0
12	ሰሜን ሸዋ	6	3,094,275.83	0.54	4	2,943,641.61	0.71
13	ዋግ ኽምራ ብሔረሰብ						0
14	ኦሮሞ ብሔረሰብ						0
	ድምር	29	569,589,919.15	100	68	412,805,098.75	100

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 337 መ/ቤቶች

ውስጥ በ68 መ/ቤቶች ብር 412,805,098.75 ባለው የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መሰረት ገቢ በወቅቱ ሳይሰበሰብ በውዝፍነት ተገኝቷል። ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግስት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ማዕከላዊ ጎንደር ብር 129,701,242.19 (31.42%)፣ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ብር 218,912,512.60 (53.03) እና ምስራቅ ጎጃም ዞን ብር 44,436,278.05 (10.76) ፣ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ::

መንግስት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን ከተሰጣቸው መ/ቤቶች ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደውን በታሳቢነት በመያዝ መሆኑ ይታወቃል:: ስለሆነም ገቢን በወቅቱ መሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል። ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ገንዘብ ዉስጥ በ6 መ/ቤቶች ብር 50,437,941.74 (12.22%) የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀልን ሲሆን ቀሪው ብር 362,367,157.01 (87.78%) በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2015 ዓ/ም ድረስ ስለመሰብሰቡ ግብረ-መልስ አልተሰጠም። (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)::

1.6.1. ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፤

በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 194,423.63 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል። ገቢው ከየሚመለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ ያልተገለፀ በመሆኑ ያልተሰበሰበው የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም።

1.6.2.ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች፣

ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ48(14.24%) መ/ቤቶች ብር 916,031,374.02 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም።

የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች ባህር ዳር ከተማ አስ/ገቢዎች መምሪያ ብር 575,074,611.28 የያዙ 955.52 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ጎንደር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 308,956,988.18 የያዘ 581 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ መሰበሰሳቢያ ደረሰኞች፣ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 6,662,400.62 የያዘ 255.36 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ደሴ ከተማ ፍርድ ቤት ብር 6,341,753.39፣ጃቢ ጠህናን ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 5,772,437.00 የያዘ 362 ጥራዝ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ግብር መሰብሰቢያ፣ሳይንት ወረዳ የመጀመሪያ ደ/ሆስፒታል ብር 2,766,859.38፣እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 971,161.57 የያዘ 233.24 ጥራዝ የመደበኛና የስፖርት ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ጎዛም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 931,181.42 የያዘ 270.23 ጥራዝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች፣ደሴ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 840,655.93፣ደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር 821,880.68፣ደሴ ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 734,037.39፣አዋበል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር

640,458.00 የያዘ ገቢ መሰሰቢያ፣ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 468,199.88 የያዙ 98.68 ጥራዝ የእንስሳት ጤና እና 38.56 ጥራዝ የመደበኛ ገቢ እና እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 454,801.33 የያዘ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ስራ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ገቢውን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን፣ከብር 450,000.00 በላይ የያዙ ደረሰኞች ለኦዲት ባለማቅረብ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡

ይህም ለኦዲት ስራ ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሁን አይሁን ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ካልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ባሳሰብነው መሰረት በ1 መ/ቤት ብር 141,713.00(0.02%) የያዘ ደረሰኝ ቀርቦ የተረጋገጠ ሲሆን በቀሪው ብር 915,889,661.02 (99.98%) ላይ የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ሰኔ 24/2015 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

1.7. የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት፤

1.7.1. በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች ውስጥ በ140 መ/ቤቶች ብር 4,248,867,738.87 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ)ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

ሠንጠረዥ-7 በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ሂሣብ፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2013 ሂሣብ			2014 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1.	የክልል መ/ቤቶች	13	1,449,573,661.94		45	2,561,867,358.77	60.29
2	ባህር ዳር ከተማ	1	39,434,348.30		1	29,319,990.69	.70
3	ምዕ/ጎጃም	7	108,181,620.60		18	266,409,065.73	6.27
4	ምስ/ጎጃም	6	383,984,879.64		17	276,606,822.37	6.51
5	ማዕከላዊ ጎንደር	1	47,746,727.52		9	398,772,691.78	9.39
6	ሰሜን ጎንደር	2	40,078,669.98		3	32,444,440.61	.76
7	ምዕራብ ጎንደር	1	7,402,676.62		6	21,384,317.86	.50
8	ደቡብ ጎንደር	7	115,645,152.43		14	200,476,643.07	4.72
9	አዊ ብሔረሰብ	8	110,666,990.71		10	138,184,434.36	3.25

10	ሰሜን ወሎ				2	121,427,972.66	2.85
11	ደቡብ ወሎ				5	101,465,849.43	2.39
12	ሰሜን ሸዋ	2	17,910,502.89		10	100,508,151.54	2.37
13	ኦሮሞ ብሄረሰብ				-	-	
14	ዋግሽምራ ብሔረሰብ				-		
ድምር		48	2,320,625,230.63	100	140	4,248,867,738.87	100

በአጠቃላይ በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 2,320,625,230.63 ጋር ሲነፃፀር በ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ92 እና በገንዘብ መጠን በብር 1,928,242,508.24 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በወቅቱ ያልተሰበሰበ /ያልተወገደ/ ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የአስተዳደር እርከኖች ውስጥ በወቅቱ ያልተሰበሰበ/ያልተወገደ/ ከፍተኛ ተሰብሣቢ ሂሣብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 1,135,016,631.83፣አብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ብር 374,687,079.38፣ አብክመ ግብርና ቢሮ ብር 283,326,327.53፣አብክመ ትምህርት ቢሮ-2013 ብር 197,811,907.69፣አብክመ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 170,512,623.19፣ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 139,307,584.71፣ወልዲያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 114,148,170.68 ፣ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 82,403,532.58፣ አብክመ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ ብር 81,944,830.93፣ጎንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 71,293,699.90፣ አብክመ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ብር 59,735,369.69 ፣ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 53,342,001.40፣ኮቦልቻ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 53,270,611.19፣ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 49,437,664.27፣አብክመ ትምህር ቢሮ-2014 ብር 49,086,244.17፣ ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 47,019,143.26፣አብክመ መንገድ ቢሮ ብር 44,005,567.00 እና ጃቢ ጠህናን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 42,778,373.42 ፣ከ40 ሚሊዩን በላይ የተሰብሳቢ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ ወይም ከመዝገብ የመሰረዣ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በቁጥር 6/2004 በክፍል-4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ገልጸናል፡፡

ይህም ሂሳብ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት ብር 49,676,295.36(1.17%) የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 4,199,191,443.51 (98.83%) ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ አልተገለፀም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ከሚሰበሰብባቸው አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ30 መ/ቤቶች ብር 240,971,186.71 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡ ከእነዚህ ተሰብሳቢ ሂሣቦች መካከል ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 58,652,082.50፣ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 31,270,998.28፣እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 22,306,779.97፣ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 16,923,715.70፣ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 16,908,591.32፣ ጎዛምን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 12,409,431.73፣ላሊበላ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 12,206,544.85፣ ሞጣ ከተማ አሰ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 11,945,381.65፣ እነብሴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 11,496,018.24፣ ደጀን ከተማ ነ/ፋይ/ድ/ማዕከል ብር 11,402,197.98፣ቢቡኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,662,293.23 እና ደባይ ጥላት ግን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 10,241,807.11፣ከ10-ሚሊዮን በላይ የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ ያልተገኘላቸውን ተሰብሳቢዎች በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡

ይህም ሂሳብ ትክክለኛ ተሰብሳቢና ባለቤት ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ መ/ቤቶቹ ተሰብሳቢው ሂሳብ የተያዘበትን አግባብ በማጣራት በሚገኘው ውጤት መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ በሪፖርት ያስገነዘብን ቢሆንም የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

1.7.2. በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ33 መ/ቤቶች
ብር 1,829,855,394.64 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመኖሩ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመቅረቡ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

ሠንጠረዥ-8 በተቀጽላ ሌጀር ያልተመዘገበ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

ተ.ቁ.	በክልል ማዕከላትና ዞን	የመ/ቤቱ ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	9	1,722,066,145.99	94.11
2	ባህር ዳር ከተማ		-	

3	ምዕራብ ጎጃም	1	9,501,643.67	.52
4	ምስራቅ ጎጃም	7	**34,751,945.85**	1.90
5	ማዕከላዊ ጎንደር	2	**8,554,878.73**	.47
6	ሰሜን ጎንደር	-	-	
7	ምዕራብ ጎንደር	2	2,828,496.02	.16
8	ደቡብ ጉንደር	6	49,467,509.79	2.70
9	ሰሜን ወሎ	1	14,398.99	0
10	ሰሜን ሸዋ	2	2,337,368.91	.13
11	ደቡብ ወሎ	1	208,267.45	.01
12	ኦሮምያ ብሔረሰብ ዞን	0	0	
13	አዊ ብሔረሰብ ዞን	1	88,029.30	00
14	ዋግኽምራ	1	36,709.94	00
	ደምር	33	1,829,855,394.64	**100**

የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 1,669,292,605.60፣ሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 28,333,309.56፣እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 25,019,389.95፣አብክመ ትምህርት ቢሮ-2013 ብር 21,941,522.97፣ስማዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 21,692,044.50 እና እናርጅና እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 14,458,486.59፣አዋበል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 13,725,829.19፣ ከብር 10 ሚሊዮን በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ ገላጭ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ ወይም ከመዝገብ ለመሰረዝ የማያስችል በመሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በየስሙ ተለይቶ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ከመዝገብ ሊሰረዝ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ (አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

1.8. የወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋናዋና የወጪ ሂሳብ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.8.1 የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት *የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣*

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ8 መ/ቤቶች ብር 16,426,976.22 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና የአፈፃፀም ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 13,565,113.45 የአርጡማ ፉርሲ ሆስፒታል ለመገንባት በወጣው ጨረታ መሰረት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው አለም ፀሐይ ጫኔ ድርጅት ሆኖእያለ ከፍተኛ ዋጋ የአቀረበው አቢታ ኮንስትራክሽ ድርጅት ጨረታውን እንዲያሸንፍ ተደርጎ የተመረጠ እና ግዥው የተፈፀመ በመሆኑ በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት እና ይህው የግንባታ ግዥ በሚመለከተው የፍትህ አካል የውል ስምምነቱ ተመርምሮ ሳይፀድቅ የተፈፀመ መሆኑ፣
- አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ብር 2,188,044.04 ለዘጌ መካከለኛ ሞገድ ማሰራጫ ጣቢያ ትራስሚተር የማይክሮ ዌቭ ሊንክ ሴት ግዥ ተፈጽሞ ንብረቱ ገቢ ሲደረግ የዚሁ እቃ አንቀሳቃሽ ዋና ክፍል የሆነው ማይክሮ ዌብ ሊኩ እንደማይሰራ እየታወቀ በሙያተኞች እንደሚሰራ ተደርጎ ማረጋገጫ የተሰጠበት እና ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ተደርጎ የተፈፀመ የማይሰራ እቃ ግዥ፣
- ጃዊ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 274,395.00 የገንዘብ ጽ/ቤት ተሽከርካሪ የሆነች ኮድ 35-ዕድ-1440 በመስክ ላይ ብልሽት የገጠማት እና ለጥገና አቶ ሰለሞን ጋራዥ የገባች ሲሆን በጋራዥ ውስጥ በቆየችበት ወቅት የተሽከርካሪዋ የተለያዩ የውስጥ እቃዎች ተፈተው የተወሰዱ በመሆኑ በመንግስት ላይ የደረሰ የገንዘብ ጉዳት ብር 262,395.00 እና በጤና ጥብቃ ጽ/ቤት የውሎ አበል በጀት ተረፈ በሚል 3-ግለሰቦች መስክ ወጥተው ስራ ሳይሰሩ እንደሰሩ ተደርጎ ሰነድ በማዘጋጀት እያንዳንዳቸው ብር 4,000.00 ወጭ በማድረግ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ላፕቶፕ ኮምፒውተር ግዥ ተፈጽሞ የተሰጠው ሲሆን ይህውም ላፕ ቶፕ ኮምፒውተር በመንግስት ንብረትነት ሳይመዘገብ የቀረ እና ግለሰቡ በግል ይዞ እየተጠቀመበት የተገኘ ብር 12,000.00፣
- ቡሬ ከተማ አስ//አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 161,500.00 ለመንገድ ስራ አገልግሎት የሚውል በቢያጆ ጠጠር በተደፋ ቁጥር ኩፖን እየቀረበ ክፍያ እንዲፈጽም በሚል ትዕዛዝ በተወካይ ረዳት ገንዘብ ያዥ የግል አካውንታቸው የመንግስትን ገንዘብ ገቢ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አገልግሎቱ ሳይገኝ እና ክፍያው ሳይፈፀም ለግል ጥቅም ውሎ የተገኘ ሂሳብ፣
- ባህር ዳር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 128,410.97 በአለም ባንክ የበጀት ድጋፍ የህዝብ ሻወር እና መፀዳጃ ቤት ግንባታ በቀበሌ 11፣13 እና 14 ለተገነባበት የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ከተከፈለ በኋላ የሳይት ለውጥ ተደርጓል በሚል ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ የተቋረጠ እና ግንባታው በአካል ሲታይ የሌለ ሆኖ የተገኘ ክፍያ፣
- ደሴ ከተማ ገንዘብ መምሪያ ብር 59,912.76 ለቦሩ ስላሴ ገበሬዎች ማሰልጠኛ አገልግሎት የሚውል በሚል አሸዋና ጠጠር ሳይገዛ የተገዛ በማስመሰል የርክክብ ቬርቫል በማቅረብ ሂሳቡ የተወራረደ እና ምንም አይነት የግንባታ ስራ ሳይከናወን ገንዘቡ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣

- እንሳሮ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ብር 42,850.00 በቁጥር 101 ቆርቆሮ፣95 ኪሎ ምስማር እና 41 ኩንታል ስሚንቶ ግዥ ሳይፈጸም እንደተገዛ በማስመሰል የንብረት ገቢ ደረሰኝ በአየር ላይ በማስቆረጥ ተወራርዶ የተገኘ ሂሳብ፣
- አድማስ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር ዩኒየን ብር 6,750.00 ዩኒየኑ የግብዓት ማከማቻ መጋዘን በጨረታ አወዳድሮ ሲከራይ አሸናፊው ግለሰብ በጨረታ ከአሸነፈበት ዋጋ በላይ ውለታ በመያዝ ክፍያው የተፈፀመ እና ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ሰራተኛ የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊው በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ለፍትህ አካላት ያሳወቅን ቢሆንም እስከ ሰኔ 24/2015 ዓ.ም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልተገለፀልንም፡፡

1.8.2. ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

በ3መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 914,045.87 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ እነሱም፡-
አብክመ ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 753,571.01፣ሲያደብር ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 84,781.07 እና ምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 75,693.79 ናቸው፡፡

ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉ ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ (ስራ ተቋራጮች) እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በትኩረት ሊሰራ ይገባዋል፡፡

1.8.3. አለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ፣

ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ109 (32.34%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞ የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 10,406,426.44 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡--

ሠንጠረዥ-9 አላግባብ የተፈፀመ ክፍያ ፣

ተ/ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2013 ሂሣብ			2014 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	ገንዘብ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	ገንዘብ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	7	1,163,714.68		30	2,268,113.79	21.80
2	ባሕር ዳር ከተማ				1	7,900.00	.08
3	ምዕ/ጎጃም	3	49,382.60		8	368,396.84	3.54

4	ምስራቅ ጎጃም	6	2,200,320.49		19	1,679,881.92	16.14
5	ማዕከላዊ ጎንደር`	2	82,550.84		7	1,919,795.49	18.45
6	ሰሜን ጎንደር	3	158,452.71		2	441,707.72	4.24
7	ምዕራብ ጎንደር	1	43,539.23		5	533,692.25	5.13
8	ደቡብ ጎንደር	5	1,891,064.27		8	553,578.54	5.32
9	አዊ ብሔረሰብ	6	1,850,158.76		7	364,026.08	3.5
10	ደቡብ ወሎ	1	45,537.20		9	1,072,560.67	10.31
11	ኦሮሞ ብሔረሰብ				1	4,673.39	.05
12	ሰሜን ሸዋ	4	334,347.44		11	968,815.00	9.30
13	ሰሜን ወሎ				0	0	0
14	ዋግኽምራ ብሔ/				1	223,284.75	2.14
	ድምር	38	7,819,068.22		109	10,406,426.44	100

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 200,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **አምባ ጊዮርጊስ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,236,100.92፡-** በተመሳሳይ ቀን በድጋሜ እና ከአበል አከፋፈል መመሪያ ውጪ ለመንግስት ሰራተኛ ላልሆኑ ግለሰቦች የሰላም አስከባሪ በሚል የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ፣የማሽነሪ ኪራይ ክፍያ ሲፈፀም ማሽኖቹ ስለመስራታቸው ማስረጃ ሳይቀርብ እና ላልተሰራ ስራ አላግባብ የተከፈለ ሂሳብ፣
- **አብክመ ትምህርት ቢሮ-2014 ብር 901,049.76፡-** በተለያዩ ወረዳዎች የት/ቤት ግንባታ ለተከናወነበት የተለያዩ ዙሮች ክፍያ ከተሰራ ስራ ውጭ አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ፣ በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣ከውለታ ውጭ የተከፈለ የመፃህፍት ዝግጅት ክፍያ፣
- **ደሴ ከተማ አስተዳደር ገንዘብ መምሪያ ብር** 766,325.00:- የደሴ ከተማ ግብርና መምሪያ ለጢጣ ገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ እና ለጢጣ ቀበሌ አባጃጅ የመስኖ ካናል ግንባታ ለማከናወን 528.5 ኩንታል ስሚንቶ ግዥ የተፈፀመ ሲሆን ስራው ያልተጀመረ እና ከስድስት ወር በላይ በመጋዝን እንዲቀመጥ በመደረጉ ለብልሽት የተዳረገ የስሚንቶ ሂሳብ፣
- **ምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 523,033.51፡-** ቆላ ድባ ከተማ በተሰጠ ስልጠና በከተማው የሚሰሩ ሰራተኞች ከተለያዩ ቀበሌዎች እንደመጡ ተደርጎ በድጋሜ እና ቀን በመጨመር አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፤
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 408,217.50፡-** ወደ ቀበሌ ለስራ መስክ ወጥተዋል በሚል በድጋሜ የተከፈለ የውሎ አበል እና የስልጠና አበል፣የኮንትራትም ሆነ ቋሚ ቅጥር ሳይፈጸም

ለደመወዝ እና ለነዳጅ የተከፈለ፤ በጎንደር ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ለቆዩ አመራር ስራ ሳይሰሩ ከመመሪያ ውጪ ለውሎ አበል እና ትራንስፖርት የተከፈለ ፤

- **እንጅባራ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር** 407,800.00፡- በሆስፒታሉ የቲቢ ማዕከል የብሎክ ግንባታ ለማስግባት በወጣው ግልጽ ጨረታ መሰረት ለአሸናፊው የስራ ተቋራጭ ከመመሪያ ውጭ አላግባብ የተሰጠ ብድር እና የስራ ተቋራጩ ግንባታውን አቋርጦ በመሄዱ ያልተመለሰ የመንግስት ገንዘብ፣
- **እናርጅና እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 389,296.19፡- በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ወፊት 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት፣አባ ጀንበር 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት፣እነሚ ደብረዘይት 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት፣በአጋምና 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት እና በደብረ ወርቅ ከተማ መናህሪያ አጥር ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ ክፍያ፣
- **ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 375,776.50፡- ሰራተኞች ለስራ መስክ እና ለስልጠና ለወጡበት ክፍያ ሲፈፀም ከመደበኛ እና ከዕርዳታ ሂሳቦች በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ እና በብልጫ የተከፈለ ክፍያ ፣
- **አብክመ ትምህርት ቢሮ**-2013 **ብር** 336,629.39፡- በሰሜን ሸዋ ዞን በሞረትና ጅሩ ወረዳ የበጣሶ 2ኛደረጃ ግንባታ የመጀመሪያ ዙር ፣በመዝ ማማ ምድር ወረዳ የቆሎ ማርገፊያ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዙር፣በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ተስፋ 2ኛ ደ/ት/ቤት የመጀመሪያ ዙር፣በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ወገራ ወረዳ ውስጥ ትርጎስጌ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የቤተመፅሀፍት ህንፃ ግንባታ 4ኛ ዙር ክፍያ ፣በሰቆጣ ቃል ኪዳን ተራድኦ በጀት የዳስ መማሪያ ክፍሎች ወደ ቡሉኬት ግንባታ ለመቀየር የመጨረሻ ዙር ፣በደቡብ ወሎ ዞን በደሴ ዙሪያ ወረዳ የበረራ ገተራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ የመጨረሻ ዙር፣በጃናሞራ ወረዳ እንጨት ካብ 2ኛ/ደ/ት/ቤት የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ ክፍያ፣
- **ሞረት እና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 324,873.35፡- አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ፣
- **ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 241,127.50፡- አላግባብ የተከፈለ የአገልግሎት ጥገና ግዥ፣ በድጋሜ የተከፈለ ውሎ አበል፣በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣አላግባብ የተከፈለ የስልክ ወጪ እና ከበጀት አመቱ ውጪ ተከፍሎ የተገኘ የውሎ አበል ሂሳብ፣
- **ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 223,284.75፡- ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ በስራ ቦታቸው እያሉ እና ስልጠና ለመሳተፋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ፣
- **ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር** 200,580.22፡- ስልጠና ለመሳተፋቸው ማስረጃ ሳይቀርብ፣ ለግንባታ ስራ ክፍያ ሲፈፀም ከተሰራው በላይ በብልጫ የተከፈለ እና መስክ ለስራ ሳይወጡ እንደተወጣ ተደርጎ የተከፈለ፤
- **ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል**-2013 **ብር** 200,036.00፡- በድጋሜ የተከፈለ፣መከፈል ካለበት በላይ የተከፈለ፣ሰራተኞች ስልጠናውን ለመሳተፋቸው ማስረጃ ሳይኖር እና ከሚከፈለው ታሪፍ በላይ የተከፈለ ውሎ አበል፣

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ይህ ሪፖርት እስተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ ብር 198,355.31 የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 10,208,071.13 በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

1.8.4. የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ23(6.82%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 14,842,625.51 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- ፎገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል-2013፡-በወረዳው መንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ከአልበር እስከ ኪንቲ መንገድ ለተሰራበት ክፍያ ሲፈፀም የግንባታ ስራው በትክክል ለመሰራቱ በባለሙያ የተረጋገጠበት ማስረጃ እና የመንገድ ስራው ተሰርቶ የተጠናቀቀ ለመሆኑ የርክክብ ሰነድ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ ብር 3,235,101.48፣
- አብክመ ግብርና ቢሮ፡- በኢፋድ እና በክልሉ የገንዘብ ድጋፍ የቡርቃ ወንዝ መስኖ ግንባት ተፈጽሞ የ6ኛ እና 7ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የግንባታ የስራ ስፍር ልኬት take off sheet /ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ 2,535,186.90፣
- ዱር ቤቴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- ለወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ቢሮ ሲገነባ፣ቀበሌ 01 ሚካኤል ሰፈር ለተሰራው የዲችና የቦይ ግንባታ፣በቀበሌ 01 ልምጭ ወንዝ እስከ አያሌው መኮነን ትምህርት ቤት የዲች ቦይ ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት/take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ብር 2,144,895.53፣
- ደንበጫ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- በከተማ አስተዳደሩ የኮበል እስቶን ንጣፍ የመሬት ዝግጅት ስራ ለተሰራበት ክፍያ ሲፈፀም ጊዜያዊ ርክክብ ሳይፈፀም የተከፈለ የመጨረሻው ዙር ክፍያ ብር 1,216,987.92፣
- አብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፡- ለባህር ዳር ፍሬሽ ፍሩት ፕሮጀክት አገልግሎት የሚውል የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ተከናውኖ ክፍያ ሲፈጽም የስራ ስፍር ወረቀት / take off sheet /ሳይቀርብ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሳይፈፀም የተከፈለ ክፍያ ብር 1,096,883.96፣
- እናርጅና እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ለሚገነባው ወፌት 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት፣አባ ጀንበር 1ኛ/ደረጃ ት/ቤት፣እነሚ ደብረዘይት 1ኘ/ደረጃ ት/ቤት የመጨረሻ ዙር እና የወረዳው መንገድና ትራስፖርት ጽ/ቤት በደብረ ወርቅ ከተማ መናኸሪያ የአጥር ግንባታ ሲፈጸም ከ1-3ኛ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 1,087,907.85፣

- እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- የመንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ከጉና ጉና ድቦ እና ከጉና ጉና በርሳይ ድረስ የመንገድ ስትራክቸር ግንባታ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈጸም የተሰራውን ስራ የሚያሳይ የግንባታ ስራ ስፍር ልኬት ወረቀት / take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 834,378.62፣
- ጠዳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፡- የመማሪያ ክፍሎች በርና መስኮት፣የኮሌጁ ክበብ እና አዳራሽ የፊኒሽንግ ስራ ለተራበት ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት/take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 495,263.13፣
- አብክመ ትምህርት ቢሮ-2014 ፡- በሰሜን ወሎ ኮን ላስታ ወረዳ ለሚገነባው የእንጃፍት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በእስቴ ወረዳ ለሚገነባው የወቃቸት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣በሰዴ ሙጃ ወረዳ ለሚገነባው የአዲስ አለም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ባህር ዳር ከተማ ለሚገነባው የልደታ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣በደቡብ ሜጫ ወረዳ ለሚገነባው የናኒ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት እና በተንታ ወረዳ ለሚገነባው የፊጦ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት /take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 491,749.62፣
- አብክመ ትምህርት ቢሮ-2013 ፡- ቡሬ ዙሪያ ወረዳ የአለፋ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣በቋራ ወረዳ የቴወድሮስ ከተማ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት ወረቀት/take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 479,015.08.፣
- አንካሻ ጓጉሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- የወረዳው መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ላስገነባው የግምጃ ቤት መናኸሪያ አጥር ግንባታ የመጀመሪያ ዙር እና የመጨረሻ ዙር ክፍያ ሲፈፀም የስራ ስፍር ወረቀት/take off sheet/ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 294,610.84፣
- ጃናሞራ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት፡-በትምህርት ጽ/ቤት ለመካነ ብርሀን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሊሾ ስራ ሲሰራ፣በውሃ ጽ/ቤት ከዋሽ ሂሳብ ለሳቅባ ቀበሌ ግርዳገቦ ጎጥ መጨኤ፣በትዕዛዝ ቀበሌ ላይ ፎቅፎቅ ጎጥ፣ለደሮ ቀበሌ ሹርታው ጎጥ እና ደንቆከ ቀበሌ ድብላ ጎጥ ምንጭ ማጎልበት ስራ ለተከናወነበት እንዲሁም በሲቪል ሰርቪስ ፑል የመሰብሰቢያ አዳራሽ እስቶርና የቢሮ ግንባታ ሲፈፀም የስራ ስፍር ልኬት /take of sheet/ ሳይቀርብ የተከፈለ ክፍያ ብር 293,004.41፣

እነዚህ ከብር 250,000.00 በላይ ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት እና ጊዜአዊ ርክክብ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል በስራ ዝርዝሩ መሰረት ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች ባሳሰብነው መሰረት የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ የተተካ ወይም ተገቢው ማስረጃ የቀረበለት ሂሳብ ብር 1,109,208.01 ሲሆን ቀሪው ብር 13,733,417.50 በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከ ተሠራበት ሰኔ 24/2015 አልተገለፀም፡፡

1.8.4. ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤

ማንኛውም ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ20(5.93%) መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 7,939,701.65 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ-10 ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፣

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	2013 ሂሣብ			2014 ሂሣብ		%
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	
1	የክልል መ/ቤቶች	3	1,957,015.91		4	293,194.38	3.69
2	ባህር ዳር					0	0
3	ምዕራብ ጎጃም				2	945,953.96	11.91
4	ምሥራቅ ጎጃም				4	642,376.05	8.10
5	ማዕከላዊ ጎንደር				2	1,228,648.46	15.47
6	ሰሜን ጎንደር				1	317,486.57	4
7	ምዕራብ ጎንደር				2	604,103.28	7.62
8	ደቡብ ጎንደር	1	11,696.00		2	3,884,399.00	48.92
9	አዊ ብሔረሰብ	1	18,412.90		1	2,600.00	.03
10	ደቡብ ወሎ				1	17,940.00	.23
11	ኦሮሞ ብሔረሰብ					0	0
12	ሰሜን ሸዋ	2	344,169.90		1	2,999.95	.03
13	ሰሜን ወሎ					0	0
14	ዋግኽምራ ብሔረሰብ						
ድምር		7	2,331,294.71		20	7,939,701.65	100

በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር 2,331,294.71 ጋር ሲነፃፀር በ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር በ13 እና በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 5,608,406.94 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ በመ/ቤቶች ችግሩ እየጨመረ መምጣቱን የሚያመላክት ሲሆን ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 3,388,674.00፣ምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፈ/ድ/ማዕከል ብር 830,207.06፣የቡሬ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 776,990.91፣አዋበል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 552,815.00 እና መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 519,000.00 በመያዝ በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ችግሩ ገዝፎ ከብር 500,000.00 በላይ የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ስለሆነም ክፍያውን የፈፀሙት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ማግኘታቸውን የማያመላክት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ ወይም ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት ባሳሰብነው መሰረት ብር 11,218.85 ይህ ጥንቅር እስከ ተሠራበት ሰኔ 24/2015 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 7,928,482.80 በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልተገለፀልንም፡፡

1.8.5. ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣

ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ9(2.67%) መ/ቤቶች ብር 29,148,709.87 የያዙ የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር ተረጋግጦ በግብረ መልስ እንዲገለጽ ብናሳስብም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም፡፡ ከዚህም ውስጥ ከብር 300,000.00 በላይ ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

አብክመ ትምህርት ቢሮ-2014 ብር 23,828,843.94፣ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,938,755.80፣ ቋሪት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,903,373.13፣ ጃዊ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 996,232.26 እና ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 318,231.01 ዋና ዋናወቹ ናቸው፡፡ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ስራ ሊቀርብ ባለመቻሉ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ማስረጃዎቹ ተገቢ ክፍያ እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

1.8.6. የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሳብ ፤

የዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው የግዥ መመሪያ መሰረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና የዋጋ ቅናሽ ለመገኘቱ እና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ55 (16.32%) መ/ቤቶች ብር 46,599,847.46 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ አፈፃፀም ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ-11 **የግዥ ስርዓትን ያልተከተለ፣**

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2013 ሂሣብ			2014 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የግንዘብ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የግንዘብ ልክ	%
1.	የክልል መ/ቤቶች	10	14,549,731.62		22	25,270,458.93	54.23
2.	ባህር ዳር				-	-	0
3.	ምዕራብ ጎጃም	2	1,199,951.90		4	2,135,638.34	4.6
4.	ምስራቅ ጎጃም	3	980,681.44		9	**4,139,078.32**	8.88
5.	ማዕከላዊ ጎንደር				3	**1,382,275.76**	2.97
6.	ሰሜን ጎንደር	1	102,382.79		1	**16,212.72**	.03
7.	ምዕራብ ጎንደር	1	30,816.30		2	1,514,218.93	3.25
8.	ደቡብ ጎንደር	3	1,240,056.67		2	**5,808,018.50**	12.46
9.	አዊ ብሔረሰብ	2	575,932.45			0	0
10.	ደቡብ ወሎ	1	169,800.00		5	531,514.84	1.14
11.	ኦሮሞ ብሔረሰብ				2	487,805.43	1.05
12.	ሰሜን ሸዋ	2	527,734.56		4	4,420,725.69	9.48
13.	ሰሜን ወሎ				1	893,900.00	1.91
14.	ዋግኽምራ ብሔረሰብ				-	0	0
	ድምር	25	19,377,087.73		55	46,599,847.46	100

የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው መ/ቤቶች፡-

- አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ብር 9,634,000.00፡- 3ባለ 30KVA እና 2 ባለ-400 KVA ጀነሬተር ግዥ ለመፈፀም እስፔሲፊኬሽን ወጥቶ ከእስፔሲፊኬሽን ውጭ 3ባለ 33KVA እና 2ባለ 400KVA ግዥ ተፈጽሞ ነገር ግን በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት እንደቀረበ ተደርጎ የባለሙያ ማረጋገጫ ቀርቦለት ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የሆነ ግዥ፣

- እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 5,580,000.00፡- የወረዳው መንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ከእብናት አምባጨኮ፣ከእብናት ዋራብ እና ከሰለማያ ኒቆራ መንገድ ለማሰራት የዶዘር፣የግሪደር፣ የኤክስካቫተር በጃክ ሀመር እና የኤክስካቫተር በአካፋ የማሽነሪ ኪራይ ግዥ ለመፈፀም ግልጽ ጨረታ ወጥቶ 2-ተጫራቾች ብቻ በተሳተፉበት ሁኔታ ከግዥ መመሪያ ውጭ የተፈፀመ ግዥ፣
- አብክመ ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 3,037,150.66፡- የግቢው አጠቃላይ እድሳት ሲደረግ፣ ብሪጅስቶን የመኪና ጎማ ግዥ ሲፈፀም፣የተሽከርካሪዎች ጥገና ሲካሄድ አሳማኝ ምክንያት ሳይኖር በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እንዲሁም የጀኔሬተር ሲልድ ባትሪ ግዥ፣የዲስክ ቶፕ ኮምፒውተር እና የፕሪተር ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን የልዩ ኃይል ፖሊስ ዘርፍ ብር 2,856,243.50፡- የጀነሬተር ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 2,306,499.54፡- የመኪና ጎማ እና የቢሮ ፈርኒቸር ግዥ በግልጽ ጨረታ ግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባው በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እና የጎማ ግዥ ሲፈፀም የውል ስምምነቱ በፍትህ አካላት ሳይፀድቅ የተፈፀመ፣
- አለም ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,835,580.00፡-የከተማ አሰተዳደሩ ቤቶችና ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት (G+2) ፎቅ ሙሉ በሙሉ የሚያንቀሳቅስ CGM60KVA 50 HZ የሆነ የጀኔተር ግዥ ሲፈጽም በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባው ያምንም አሳማኝ ምክንያት በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ እና የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቱ የመኪና ጎማ ከነካላማዳሪው ግዥ ሲፈጽም ግዥው በፍትህ አካል ሳይጸድቅ የተፈፀመ ግዥ፣
- **አብክመ ገቢዎች ቢሮ ብር 1,479,205.64፡-** የቢሮው አትክልት ቦታ የአጥር ግንባታ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲኖርበት አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በውስን እና በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ እንዲሁም የጃንቦ ኬንት ግዥ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ሲፈፀም ጨረታ ሰነዱን ሞልተው ያልመለሱ ተጫራች መሳተፍ ያልፈለጉበትን ምክንያት የገለጹበት ማስረጃ ሳይያያዝ ቀሪ ተጫራቾችን አወዳድሮ የተፈፀመ ግዥ፣
- አብክመ ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ብር 1,398.955.64፡- የደንብ ልብስ እና የጎማ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ በቀጥታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,390,318.93፡-የደንብ ልብስ፣የተሽከርካሪ መለዋወጫ እቃዎች፣ ለውሃ ግንባታ አገልግሎት የሚውል አፍሮዳቪ ፓምፕ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ እንዲሁም የኮፒውተር እና ሞተር ጀኔነተር ግዥ ሲፈፀም ጥራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ ግዥ፣

- እንጅባራ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 1,300,000.00፦ ለኮረና ታካሚዎች የሚሆን የኦክስጅን ፕላንት ማምረቻ በቀጥታ የግዥ ዘዴ ከጋስት ሶላር መካኒካል ኃ/የተ/የግል ማህበር ግዥው ሲፈፀም በስፔስፍኬሽኑ መሰረት ያልተፈጸመ ግዥ፤
- ጎንደር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 1,103,881.68፦ የኤሌክትሪክ እቃዎች፣የጥገና ዕቃዎች፣ የጽህፈት መሳሪያ፣የብቃት ምዘና ግብዓቶች፣የደንብ ልብስ ግዥ፣የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃ እና የጎማ ግዥ ሲፈፀም በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም ሲገባው አሳማኝ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የተፈፀመ፣
- ምስራቅ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 1,026,731.63፦ የዞኑ ግብርና መምሪያ የፍራፍሬ ግዥ ሲፈጽም ከአቅራቢው አካል ጋር የተያዘው የውል ስምምነት በፍትህ አካላት ተመርምሮ ያልፀደቀ እና ከግዥ በፊት የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ተቆርጦ የተገኘ የላፕቶፕ ኮፒውተር ግዥ፣ ከብር 1000,000.00 በላይ የግዥ አፈፃፀምን ያልተከተለ ግዥዎች የተገኘባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ መመሪያውን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት) ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች ባሳሰብነው መሰረት ብር 1,135,146.74 ላይ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን ቀሪው ብር 45,464,700.72 ላይ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ አልደረሰም፡፡

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 19,377,087.73 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ30 የጨመረ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 27,222,759.73 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግዥ መመሪያውን በመከተል በኩል ችግሮች እንዳሉባቸው ያመላክታል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

1.9 . የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

1.9.1 በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሣብ፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ118 መ/ቤቶች ብር 1,134,090,400.78 የተከፋይ ዕዳ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅት የፋይናንስ መመሪያውን ተከትሎ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል)፤

ሠንጠረዥ-12 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	2013 ሂሣብ			2014 ሂሣብ		
		የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%	የመ/ቤት ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	15	54,250,693.30		34	307,915,227.64	27.15
2	ባህር ዳር ከተማ	1	87,078,486.82		1	19,131,286.46	1.7
3	ምዕራብ ጎጃም	7	33,846,022.03		16	84,495,444.53	7.5
4	ምስራቅ ጎጃም	6	74,082,486.51		16	**133,581,744.10**	11.8
5	ማዕከላዊ ጎንደር	1	149,470,738.24		8	**231,791,015.82**	20.4
6	ሰሜን ጎንደር	2	12,083,933.38		3	13,766,427.84	1.2
7	ምዕራብ ጎንደር	1	8,920,717.82		3	44,434,529.59	3.9
8	ደቡብ ጎንደር	5	49,384,644.08		14	96,840,733.35	8.5
9	አዊ ብሔረሰብ	8	63,480,101.69		8	30,942,447.53	2.75
10	ደቡብ ወሎ		.		4	55,540,818.27	4.9
11	ኦሮሞ ብሄረሰብ				0	0	
12	ሰሜን ሸዋ	2	9,488,957.42		9	65,304,508.31	5.8
13	ሰሜን ወሎ				2	50,346,217.34	4.4
14	ዋግኽምራ ብሔረሰብ					0	
ድምር		48	542,086,781.29		118	1,134,090,400.78	100

በአጠቃላይ በወቅቱ ያልተከፈለ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር ያለበት የተከፋይ ሂሳብ ካለፈው ዓመት ብር 542,086,781.29 ጋር ሲነፃፀር በ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተገኘው በመ/ቤቶች ቁጥር በ70 የጨመረ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 592,003,619.49 ጨምሮ ተገኝቷል። ይህም በወቅቱ ያልተከፈለ ዕዳ ክምችት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የጨመረ መሆኑን ያመላክታል።

በወቅቱ ያልተከፈለ ከፍተኛ የተከፋይ ሂሳብ ከሚታይባቸው መ/ቤቶች መካከል ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 127,230,328.73፣አብክመ ግብርና ቢሮ ብር 78,847,724.93፣አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 68,036,131.79 ፣ ወልዲያ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰማዕከል ብር 44,341,634.04፣ኮቦልቻ

ከተማ አስ/ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 44,012,239.33፣ትምህርት ቢሮ-2013 ብር 42,154,266.36፣ መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 40,616,913.73፣አብክመ ንግድ ገበያ ልማት ቢሮ ብር 37,818,091.48፣ምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 36,903,844.04፣ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 34,817,181.98፣አነደድ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 32,139,081.17፣ ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 25,806,591.94፣ ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 23,419,128.47፣አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 22,114,904.82፣ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 21,753,292.72 እና ጎዛምን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 20,238,841.30 ከብር 20 ሚሊዩን በላይ የተከፋይ ዕዳ ክምችት በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡

ተከፋይ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመክፈያ ወይም ወደ ተጣራ ሀብት የሚቀየሩበት ጊዜ ስላላቸው በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ባሳሰብነው መሰረት ብር 16,656,198.39 ይህ ዘገባ ጥንቅር እስከተሰራበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ ተከፋይ ሂሳቡ የተከፈለ መሆኑ ግብረ-መልስ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው ብር 1,117,434,202.39 በምን ሁኔታ እንደሚገኝ አልተገለፀም፡፡

1.9.2 ተቀጽላ ሌጀር ያልዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ35 መ/ቤቶች ብር375,126,301.53 በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እና መቸ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ-13 **ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

ተ.ቁ.	መ/ቤት ስም	የመ/ቤቱ ብዛት	የገንዘቡ ልክ	%
1	የክልል መ/ቤቶች	17	296,670,187.04	79.1
2	ባህር ዳር		-	
3	ምዕራብ ጎጃም		0	
4	ምስራቅ ጎጃም	5	20,288,470.63	5.4
5	ማዕከላዊ ጎንደር	5	20,362,976.37	5.43
6	ሰሜን ጎንደር		0	
7	ምዕራብ ጎንደር	2	6,869,827.63	1.83
8	ደቡብ ጎንደር	5	30,173,619.71	8.04
9	አዊ ብሔረሰብ		0	
10	ደቡብ ወሎ	1	761,220.15	0.2
11	ኦሮሞ ብሄረሰብ		-	

12	ሰሜን ሸዋ		-	
13	ሰሜን ወሎ		-	
14	ዋግኽምራ ብሄረሰብ		-	
	ድምር	36	375,126,301.53	**100**

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር አለመዘጋጀትን በተመለከተ አብክመ አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር 169,157,144.53፣ትምህርት ቢሮ 2014 በጀት ዓመት ብር 53,953,230.25፣ትምህርት ቢሮ 2013 በጀት ዓመት ብር 38,018,883.01፣ሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብር 28,333,309.56 ፣ እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 22,301,420.89፣ ሸበል በረታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 13,619,183.31፣ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 8,652,129.56፣እስቴ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 7,665,482.43፣ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 7,415,697.70፣መተማ ዩሀንስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 5,722,549.53፣አንባ ጊወርጊስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 3,491,350.87 እና ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል ብር 3,375,174.27 እና ከ3,000,000.00 በላይ በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ በጥቅሉ ስለተመዘገበ ገንዘቡ ለማንና መቸ እንደሚከፈል ገላጭ ባለመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየጊዜው ክትትል እየተደረገ በየባለቤቱ ተለይቶ መመዝገብ ወይም ለሚመለከተው መከፈል ካልቻለም ወደ ተጣራ ሀብት መቀየር እንዳለበት በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ በግብረ መልስ ስላልተገለፀ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

1.10. የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት በትክክል የተዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ልዩነቶች ተገኝተዋል፡፡

ሠንጠረዥ-14 የሂሳብ ሪፖርት ልዩነቶች፤

በማነስ/በብልጫ	ጥሬ ገንዘብ	ባንክ ሂሳብ	የገቢ ሂሳብ	የተሰብሳቢ ሂሳብ	የወጪ ሂሳብ	የተከፋይ ሂሳብ	ዝውውር	የተጣራ ሀብት
በማነስ				8,764,539.85				
በመብለጥ					8,764,539.85			

በመብለጥ				569,287.00				
በማነስ					569,287.00			

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በአመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶቻቸው ላይ በየሂሳብ ዓይነቱ አላግባብ በማነስ እና በመብለጥ ሪፖርት የተደረጉ ሂሳቦች ተገኝተዋል፡፡ ይህም የክልሉንም ሆነ የአገሪቱን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በተገለጹት ሂሳቦች የገንዘብ መጠን በማዛባት ለውሣኔ ሰጪ አካላት የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ እንደሚችል ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ማስተካከያው በየደረጃው ተደርጎ የተዛባው የሂሳብ ሪፖርት እንዲስተካከል በየኦዲት ሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡ (ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመለከቱ)፡፡

1.11 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣

1.11.1 የንብረት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣

የመንግስት መ/ቤቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሂሳብ ለኦዲት ስራ ዝግጁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 271 መ/ቤቶች መካከል በ104(38.38%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ የሚያስችል አሰራር ሳይኖር ተገኝቷል፡፡ ንብረትን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ላለመቻሉ ምክንያቶች፤

- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (የእቃ መቆጣጠሪያ ካርዶች) ባለመቋቋሙ እና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም፤
- በንብረት ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረቶች ለቆጠራ አመቺ በሆነ መልኩ በባህሪ፤በእድሜና በአገልግሎት አይነት ለይቶ አለማስቀመጥ፣
- የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ በቆጠራ የሚገኘውን ብቻ ቆጥሮ ለተተኪዎች ከማስረከብ ውጭ ማስረከብ የሚገባቸውን ያህል ስለመሆኑ በውስጥ ኦዲተሮች በኦዲት ከተረጋገጠ በኋላ አለመሆኑ፤
- ንብረት ከመጋዘን ከወጣ በኋላም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እስኪውል ድረስ ሃብት መሆኑ ታውቆ አለመከታተል፤የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች የየወሩ ከወጪ ቀሪ እየታወቀና እየተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት አካል እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር መሰረታዊ ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይኖር ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ በየመ/ቤቱ እንዲተገበርና እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡(ዝርዝሩን አባሪ 2 ይመልከቱ)፤

1.11.2 የንብረት ሂሳብ ጉድለት

በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በልዩ ኦዲት አሰራር ኦዲት በተደረጉ 10 መ/ቤቶች በጉድለት ብር 10,623,805.32 መገኘቱ፤

- አድማስ የገበሬዎች ህብረት ስራ መህበር ዩንዩን ብር 6,081,703.35 የዩኒየኑ እንጅባራ ከተማ 02 ቀበሌ ንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆኑት ከ30/01/2013 እስከ 8/09/2014 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የአፈር ማዳበሪያ NPSB ሂሳብ ፣የዩኒየኑ ዚገም ወረዳ ንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆነው ከ30/02/2013 እስከ 30/09/2014ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት ዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ እና የዩኒየኑ የአንካሻ ወረዳ ንብረት ክፍል ሰራተኛ የሆነው ከ30/01/2013 እስከ 30/09/2014 ዓ.ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የአፈር ማዳበሪያ ሲመዛዘን በጉድለት የተገኘ የንብረት ሂሳብ ፤
- አብክመ ፖሊስ ኮሚሽን ልዩ ሐይል ም/ዘርፍ የጣና ክፍለ ጦር ብር 2,964,683.50 ክፍለ ጦሩ ለምግብ ማብሰያ የሚገለገልባቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች እና ለውሃ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩያ የፕላሰቲክ በርሜል እና ታንከር ገቢ እና ወጭ ፣ትልቁ ጀኔሬተር፤ትልቁ ፎቶ ኮፒ ፤ኮምፒውተር ከነ አክሰሰሪው እና ፕሪንተር ገቢ እና ወጭ ፣ለኤሌክትሮኒክስ የሚያገለግሉ ንብረቶች ፣አግዳሚ ወንበር፤ ሽልፍ፤የመመገቢያ ጠረጴዛ የመሳሰሉት የቢሮ መገልገያ እቃዎች እና የተለያዩ መገልገያ እቃዎች ሲመዛዘኑ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- ቦሩ ሜዳ ጠቅላላ ሆስፒታል ብር 885,482.68 ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ቤት ሰራተኛ ሁነው ስራ ከጀመሩበት ከመጋቢት 1/2007 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 6/2011 ዓ/ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የመድሀኒት ሂሳብ ፣ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ቤት ሰራተኛ ሁነው ስራ ከጀመሩበት ከ1/12/207 ዓ/ም እስከ 2/03/2011 ዓ/ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የመድሀኒት ሂሳብ እና ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ቤት ሰራተኛ ሆነው ስራ ከጀመሩበት ከ17/4/2011 ዓ/ም እስከ 18/06/2011 ዓ/ም ድረስ ያንቀሳቀሱት የመድሀኒት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ፣

- **ጃዊ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ብር 285,278.58** በጃዊ ወረዳ ለተፈናቀሉ ዜጎች ቤት ለመስራት በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጭ የተደረጉ የቤት መስሪያ ቁሳቁሶች በትክክል ስራ ላይ ለመዋላቸው ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ጉድለት፤
- አንዳቤት ወረዳ ጎኖ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 248,064.26 የመድሀኒት እስቶር ባለሙያ የነበሩት ከ10/7/2011-7/4/2012 ያንቀሳቀሱት የመድሀኒት ሂሳብ ሲመዛዘን ዋጋቸው ያልታወቁ ብዛት 4748 መድሀኒቶች እና የተገኘ የመድሀኒት ጉድለት፣

- አንዳቤት ወረዳ ጎኖ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር 127,012.65 የመድሃኒት እስቶር ሰራተኛ ከ12/09-25/112011 ዓ.ም ያንቀሳቀሱት የመድሃኒት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ ዋጋቸው ያልታወቁ መድሀኒቶች ብዛት 1,734 እና የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣
- አምበሳሜ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 17,100.00 መዳብ የኤሌትሪክ ገመድ ኬብል ከንብረት ክፍል ወጪ አድርገው ለመብራት ዝርጋታ ከዋለ በኃላ የተረፈውን 30 ሜትር ወደ ንብረት ክፍል መመለስ ሲገባ ሳይመለስ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- ዋድላ ወረዳ እስሳት ሀብት ተጠሪ ጽ/ቤት ብር 12,456.30 የእንስሳት ጤና ባለሙያ እና ገቢ ሰብሳቢ የነበሩት ከሐምሌ 1/2007 እስከ ሰኔ 23/10/2011 ዓ/ም ድረስ ያቀሳቀሱት ሂሳብ ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት፣
- ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ግብር ጽ/ቤት ብር 2,024.00 ከ09/01/2011-03/04/2014 ዓ.ም ድረስ የተገዙት የተለያዩ የጓሮ አትክልት ዘሮች በትክክል ለአርሶ አደሮች ወጭ ሆነው መድረሳቸው ሲመዛዘን የተገኘ የንብረት ጉድለት፣

በመሆኑም ከንብረት ክፍል ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ለፍትህ አካላት ብናሳስብም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

ምዕራፍ 2:- በኦዲት ሂደት ወቅት እርምጃ የተወሰደባቸው ግኝቶች በተመለከተ፤

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን በመደበኛ ኦዲት በተደረጉት 271 መ/ቤቶች በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት በ54 መ/ቤቶች የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ለየተቋማቱ ከመላካችን በፊት ብር 222,755,000.04 የማስተካከያ እና የማስመለስ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን ይህውም ቀደም ሲል ከቀረበው የግኝቶች አርዕስት የገንዘብ መጠን አልተካተተም፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 4,310,886.95፣
- ከውል ማዘግየትና ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 2,665,330.95፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝ ብር 696,291.95፣
- በወቅቱ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 67,222,199.65፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 5,251,397.85፣
- ላልተሰራ ስራ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ በወጭ የፀደቀ ሂሳብ ብር 23,473,818.21፣
- ከግዥ ስርዓት ውጭ የተፈፀመ ክፍያ ብር 22,561,431.48፣
- ያለግንባታ ማስረጃ የፀደቀ ወጭ ብር 20,674,058.03፣
- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የወጭ ሂሳብ ብር 4,548,078.27፣
- አላግባብ/በብልጫ ላልተሰራ ስራ የተከፈለ ክፍያ ብር 1,624,556.75፣
- በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 49,911,830.46፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ ብር 4,471,260.28፣
- የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጣራ ሀብት ብር 15,343,860.21፣ላይ ግኝቶቹ በመ/ቤታችን ከተገኙ በኋላ የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ከመላካችን በፊት ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በተሰጣቸው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት የእርምት እርምጃ የወሰዱ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩን አባሪ 3 ይመልከቱ፡፡

ምዕራፍ 3:- ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች እርምጃ አወሳሰድ

የክትትል ኦዲት ሪፖርት

3.1. እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት ዓመታት የኦዲት ውጤቶች

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመ/ቤታችን በመደበኛ ኦዲት በተደረጉ 271 መ/ቤቶች በተደረገው የክትትል ኦዲት የ2013 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርገው በተገኙ ግኝቶች ላይ በተቋማት ያለው የማሻሻያ እርምት እርምጃ አወሳሰድ ሲጣራ በ25 መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ይህ የጥንቅር ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ቀን ሰኔ 24/2015 ዓ.ም ድረስ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው ዓመት የኦዲት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.1.1. የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ውጤቶች ላይ አስተያየት ቢሰጥባቸውም እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ ግኝቶች፤

- አብክመ ትምህርት ቢሮ፡- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 352,556.92፣ የግንባታ ስፍር ልኬት ሳይቀርብ የፀደቀ ወጪ ብር 449,881.84 እና ያለማስረጃ የፀደቀ ወጪ ብር 22,340.40፣
- አብክመ ክልል ምክር ቤት፡- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 77,476.99 እና አላግባብ የተከፈለ የአልጋ አበል ብር 5,100.00፣
- አብክመ ጤና ቢሮ፡- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 178,101.69፣
- አብክመ መንገድ ቢሮ፡- በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 945,563.45 እና ባልተሰራ ስራ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 59,500.00፣
- ባህር ዳር ከተማ አስ/ገቢዎች መምሪያ፡- ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብር 698,521,067.48፣
- ባንጃ ወረዳ ፍርድ ቤት፡- ከውል ማዘግየት ያልተሰበሰበ የቅጣት ገቢ ብር 7,196.26፣
- ምዕራብ ጎጃም ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ የስልጠና እና ውሎ አበል ብር 11,970.00፣
- ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 20,732.80፣በብልጫ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 205,122.24፣ከውለታ በላይ የተከፈለ ግንባታ ሂሳብ ብር 3,895,855.95 እና ለኦዲት ስራ ያልቀረበ ደረሰኝ ብር 48,242.00፣
- ሸበል በረንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 18,796.45፣
- እናርጅና እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 41,779.44 እና አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 3,130.00፣
- ጣቁሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል ብር 21,654.00 እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝ ብር 71,380.00፣
- ማዕከላዊ ጎንደር ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 16,293.00፣አላግባብ የተከፈለ የነዳጅ ወጪ ብር 2,422.39 እና በብልጫ የፀደቀ ወጪ ብር 4,633.70፣

- ወገራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማእከል፡- የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 11,264.03፣ ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ ቅጣት ብር 12,596.87፣ለኦዲት ስራ ያልቀረበ ደረሰኝ ብር 53,320.00 እና አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 10,505.55፣
- ዳባት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 11,255.55፣ያልተሰበሰበ ከውል ማዘግየት ብር 12,596.87 እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝ ብር 53,320.00፣
- ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበለረ ብር 23,140.00
- አዲስ ዘመን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- ከውለታ በላይ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 1,452,514.67፣
- ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- ላልተሠራ ሥራ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 1,622,628.97 እና ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 32,154.30፣
- ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 102,987፣በብልጫ የተከፈለ ወጪ ብር 2,500.00 እና የስራ ስፍር ልኬት ያልቀረበለት ብር 24,450.00
- ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 4,076.15፣ባልተሰራ ስራ የተፈፀመ የግንባታ ሂሳብ ብር 51,042.19፣በብልጫ የተከፈለ ወጪ ብር 22,629.00፣አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 200,000.00 ፣የስራ ስፍር ልኬት ሳይቀርብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 709,326.35፣ለኦዲት ስራ ያልቀረበ የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ ብር 213,518.00 እና ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 34,125.16፣
- ሐይቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 19,071.71 እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝ ብር 2,047,537.93፣
- ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አለአግባብ/ብልጫ/ ላልተሠራ ሥራ የተከፈለ ሂሳብ ብር 4,447.85 እና ከውል ማዘግየት እና ከስራ ግብር ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 17,656.00፣
- ደብረ ብርሃን ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 12,445.00፣
- ሰሜን ሸዋ ዞን ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 847,418.58፣
- ባሶ ሊበን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ብር 82,314.50 እና ያልተሰበሰበ ቅጣት ብር 11,823.52 ፣
- ሞረትና ጅሩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡-አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 182,108.37 እና ከውል መዘግየት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 27,258.20፣
- ባሶና ወራና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ማዕከል፡- ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ የገቢ ደረሰኝብር 54,392.00

በመሆኑም በድምሩ ብር 712,947,201.93 በ25 መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች በወቅቱ በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ አስተያየት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሜ እያሳሰብን የፋይናንስ ግልጽ አሰራርና ተጠያቂነት እንዲጠናከር መ/ቤታችን

ከሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ጋር በትብብር የሚሰራውን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የእርምት እርምጃ በማይወስዱ እንዲሁም ምላሽ በማይሰጡ አካላት ላይ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ምዕራፍ 4:- ያለፉት አምስት ዓመታት አፈፃፀም

3.1 የዕቅድ አፈፃፀም ከ2010-2014 በጀት ዓመታት

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት መሰረት ካለው የሰው ሀይል ጋር የተጣጣመ የስራ መርሀ ግብር በማውጣት ከ2010 እስከ 20114 በጀት ዓመት ድረስ ያለው የ5 ዓመት እቅድ ክንውን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠኝጠረዥ-1፡- የአምስት አመት የዕቅድ ክንውን በአወቃቀር እርከን፤

ዓ/ም	በክልል (ማዕከል)		በዞን		ከተማ አስተ		በወረዳ		ድምር	
	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንዉን	ዕቅድ	ክንውን	ዕቅድ	ክንውን
2010	104	99	13	12	92	88	101	96	310	295
2011	115	103	12	10	71	62	108	95	306	270
2012	112	102	12	11	83	75	124	113	331	301
2013	78	40	16	6	40	34	122	58	256	138
2014	143	134	10	9	92	86	115	108	360	337
ድምር	**552**	**478**	**63**	**48**	**378**	**345**	**570**	**470**	1563	1341

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የክልሉ የኦዲት ክንውን የ2010 ሂሳብ በጀት ዓመት በቁጥር የ295 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት የነበረ ሲሆን የ2014 ሂሳብ በጀት ዓመት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ጨምሮ የ337 መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በ2014 ሂሳብ በጀት ዓመት የኦዲት ሽፋን በአሁኑ ጊዜ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር አንፃር ሲታይ 43.43% የደረሰ ሲሆን በ2010 በጀት ዓመት ከነበረው የኦዲት ሽፋን 14.24% መጨመሩ አሳይቷል፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንጻር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በጀት ለ2014 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት ከታወጀው የወጭ በጀት አንፃር ሲለካ 47% እና ከገቢ እቅድ አንፃር 17% ላይ ደርሷል፡፡

በአጠቃላይ በ5 □መታት የ1563 መ/ቤቶች ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 1341/85.80%/ መ/ቤቶች ተከናውኗል፡፡ይህም በያልሉ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው 776 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ጋር ሲነፃፀር እያንዳንዱ መ/ቤት በአማካኝ በየ1.73 ዓመት የኦዲት ሽፍን ያገኘ መሆኑን ያሳያል::

መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው መጨመር፣የክልሉ በጀት ከዓመት ዓመት እያደገ መምጣቱ በታሰበው መሠረት በመ/ቤት ቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የአካልተሃድሶ ማዕከላት፣ፍርድ ቤቶች፣ኮሌጆች እና ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን አስተያየታችንን እያቀረብን ይህ ተግባራዊ ቢደረግ በአብዛኛው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየበጀት ዓመቱ የኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ያግዛል ብለን እናምናለን።

3.2. ከ2010 -2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፤

ከ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ጀምሮ ባሉት 5 ዓመታት ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በተገኙ መረጃዎች መሠረት የዋናዋና ግኝቶች አማካይ ስሌት (Weighted-Average) ተሠርቶ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል።

ተ. ቁ	የኦዲት ግኝት	2010	2011	2012	2013	2014	ድምር	አማካኝ
1	የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ ጉድለት	3,470,452.30	252,137.96	9,198,998.71	2,275,716.10	16,271,341.95	31,468,647.02	6,293,729.40
2	የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የገቢ ሂሣብ	1,455,423.90	0	2,348,398.76	44,307.00	15,526,533.70	19,374,663.36	4,843,665.84
3	የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጭ ሂሣብ	26,537,407.04	9,484,900.60	11,118,146.21	1,990,635.99	16,426,976.22	65,558,066.06	13,111,613.21
5	አላግባብ የተከፈለ	7,869,866.10	5,678,736.69	12,243,844.63	7,819,068.22	10,406,426.44	44,017,942.08	8,803,588.42
6	ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ወጪ	69,136,212.19	16,313,768.12	45,546,545.04	5,401,665.39	14,842,625.51	151,240,816.25	30,248,163.25
7	የግዥ ስርዓቱን ያልተከተለ	69,982,706.37	29,254,400.10	58,672,995.26	19,377,087.73	46,599,847.46	223,887,036.92	44,777,407.38
8	ማስረጃ ያልቀረበበት	75,726,827.04	10,571,713.53	10,253,842.24	2,331,294.71	7,939,701.65	106,823,379.17	21,364,675.83
9	ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ	50,006,652.65	23,289,728.40	3,891,232.15	94,298,438.29	29,148,709.87	200,634,761.36	40,126,952.27
	ድምር	304,185,547.59	94,845,385.40	153,274,003.00	133,538,213.43	157,162,162.80	843,005,312.22	169,569,795.61

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር በተዘረዘሩት ዋና ዋና ግኝቶች ድክመት ይታይበታል። ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች እንደ የባህሪያቸው ተቀራራቢነት አጠቃላይ አቅጣጫው በሚከተሉት ግራፎች ተመልክቷል።

የጥሬ ገንዘብና የንብረት ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ የሚመራው በአብክመ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003፤ ደንብ ቁጥር 89/2004፤ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2004 እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት የፋይናንስና

ህጋዊነት ኦዲት የአሰራር ማንዋሎች መሰረት ነው፡፡ ጥሬ ገንዘብ በባህሪው ለተለያዩ ብክነቶችና አደጋዎች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ በመሆኑ በጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መደገፍ ይኖርበታል፡፡ ከውስጥ ቁጥጥር ስርአቶች አፈፃፀም አንፃርም ኦዲት ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በየአመቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህን ኦዲት ለማረጋገጥ ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በመዝገብ (ሌጀር) ምዝገባ እየተካሄደ በበጀት አመቱ መጨረሻ ደግሞ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ እና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላ ህጋዊ ቆጠራ መደረግና መመዛዘን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር መሰረታዊው የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ስለማይሟሉ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት የማይቻልባቸው ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየጊዜው ቁጥራቸው ቀላል አለመሆኑን ያመላክታል፡፡

የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት



ከግራፉ መገንዘብ እንደሚቻለው የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 9,198,998.71 እና በ2014 በጀት ዓመት ብር 16,271,341.95 ከአማካኙ ብር 6,293,729.40 በላይ በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ያለው የጉድለት መከሰት አዝማሚያ የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በግራፉ ከታየው ጉድለት ውስጥ በ2010 በጀት ዓመት የተተካ ብር 213,592.05 ሲሆን ብር 1,204,145.97 በፍታብሄርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝ፣በ2011 በጀት ዓመት ብር 76,388.49 በክስ ሂደት ላይ እንዳለ፣ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ ያለ ብር 4,447,186.42 እና በፖሊስ ምርመራ ሂደት ላይ ያለ ብር 1,132,398.79 ሲሆን በ2013 ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ

የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ5ዓመቱ ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ብር 19,374,663.36 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ፤



ከግራፉ መገንዘብ እንደሚቻለው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ የታየባቸዉ የኦዲት ዓመቶች በ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 15,526,533.70 ከአማካኙ ብር 4,843,665.84 በላይ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ያለው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ አዝማሚያ የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመበት የገቢ ሂሳብ ውስጥ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 21,570.00 እንደሆነ በወቅቱ የደረሰን ምላሽ ያመላከተ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

ባለፉት ዓመታት የገቢ ሂሳብ ኦዲት ወቅት የተስተዋሉት ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የገቢ ደረሰኞችን ከ--እስከ መዝግቦ አለማሰራጨትና የተሰራጨ ደረሰኝ በትክክል ተሰርቶበት ገንዘቡ ለሚመለከተው ገቢ መደረጉ ተረጋግጦ እንዲመለስ የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆኑ፣
- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ሲፈለጉ አለመቅረብ፤
- የገቢ ደረሰኞችን አበላልጦ ገቢ መሰብሰብና ከትክክለኛው ቁጥር ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግ፤

- ሰራተኞች በስማቸው ባወጡት ደረሰኝ መሰረት ገንዘብ ከተሰበሰበ በኂላ ሙሉ ለሙሉ ለሚመለከተው ዋና ገንዘብ ያዥ ወይም የባንክ አካውንት ፈሰስ ለማደረጋቸው ከስር ከስር ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ የሰበሰቡትን ገቢ በእጃቸው ማቆየት ብሎም ለግል ጥቅም አውሎ መቅረት ፣
- ጠቃሚ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በማዳከም ለመንግስት ገንዘብ ብክነት የአሰራር ክፍተት መፍጠር፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ደረሰኝ በስሙ ወጪ በማድረግ፤ የገቢ ደረሰኝ ራሱ በማዘጋጀት ፤ገንዘብ በመሰብሰብ፤ገቢን ራሱ መዝግቦ ለሚመለከተው ፈሰስ የማድረግ፤ በዚህ አሰራር ምክንያት ሁሉንም ስራ ደርቦ በመስራት (ቁጥጥር ሳይደረግበት) መፈፀሙ፣
- ደረሰኞችን (አንዱ ሕጋዊ ሌላው ሕገ ወጥ) ጎን ለጎን አሳትሞ በመጠቀምና ገቢ በመሰብሰብ በህገወጥ ህትመት የሰበሰቡትን ገቢ ለግል ጥቅማቸው ማዋል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እነዚህን እና በአጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ በተለይም የደረሰኞችን ዝውውር (በህጋዊ ርክክብ፤ የደረሰኙን ከ--- እስከ እና ሴሪ በመጥቀስ መመዝገብና ስራ ላይ የዋሉትን እየተከታተሉ ማስመለስ)፤ የገቢ አሰባሰብ ታሪፎችንና መመሪያዎችን በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ የመንግስት ገቢን ሰብስቦ ለታቀደለት ዓላማ ለማዋል ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ



ከላይ በግራፍ እንደተመለከተው የማጭበርበር ድርጊት የተፈጸመበት ክፍያ የ5 አመቱ ሲነጻጸር የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 26,537,407.04 እና የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ብር 16,426,976.22 ከአማካኙ ብር 13,111,613.09 በላይ ከፍተኛዉን ድርሻ ይዘው ይታያሉ፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት ሂሳብ የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመበት የወጭ ሂሳብ ውስጥ በ2012 በጀት ዓመት በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ ያለ ብር 766,159.10 እና በፖሊስ የምርመራ ሂደት ላይ የሚገኝ ብር 159,286.59 እንደሆነ በወቅቱ የደረሰን ምላሽ የሚያመላክት ሲሆን በ2014 ሂሳብ በተገኘው ግኝት ላይ እርምጃ ስለመወሰዱ እስከ ሰኔ 24/2014 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

አላግባብ የተከፈለ ክፍያ



- አላግባብ የተከፈዉ ክፍያ በ2012 በጀት ዓመት ብር 12,243,844.63 እና በ2014 በጀት ዓመት ብር 10,406,426.44 ከአማካዩ ብር 10,406,426.44 በላይ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያዎችን አላግባብ የመፈፀም ድርጊት የጨመረ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ



- ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈጸመ የግንባታ ወጭ በ2010 በጀት ዓመት ብር 69,136,212.19 እና በ2012 በጀት ዓመት ብር 45,546,545.04 ከአማካዩ ብር 30,248,163.25 በመብለጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ እንፃር የ2014 በጀት ዓመት ስርዓትን ያልተከተለ የግንባታ አፋፃፀም ወጭ የቀነሰ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ



የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ በመፈፀም በ2010 በጀት ዓመት ብር 69,982,706.37፣በ2012 በጀት ዓመት ብር 58,672,995.26 እና በ2014 በጀት ዓመት ብር 46,599,847.46 ከአማካዩ ብር 44,777,407.38 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙ ናቸው፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ የግዥ አፈፃፀም የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ



- ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ በ2010 በጀት ዓመት ብር 75,726,827.04 ከአማካዩ ብር 21,364,675.83 ከፍተኛ ብልጫ አለው፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የመንግስት ገንዘብ ያለበቂና አስተማማኝ ማስረጃ ክፍያ በመፈፀም በወጪ የማፅደቅ ተግባር የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ



ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የ2010 በጀት ዓመት ብር 50,006,652.65 እና የ2013 በጀት ዓመት ብር 94,298,438.29 ከአማካኙ ብር 40,126,952.27 ከፍተኛዉን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ማስረጃዎችን በአግባቡ ይዞ ለኦዲት ስራ ሲፈለጉ በማቅረብ በኩል መቀነሱን የሳያል፡፡

በወጪ ሂሳቦች ላይ በአብዛኛው የሚስተዋሉ ዋና ዋና ግኝቶች፡

- በክፍያና ደረሰኞች ላይ ስርዝ ድልዝ ማድረግና ከቀረበ ማስረጃ /ደረሰኝ/ በላይ ሂሳብ አበላልጦ ማወራረድ፣
- ሰራተኞች በሚሰሩበት ከተማ ለተሰጠ ስልጠና ስልጠኛው ሌላ ቦታ እንደተሰጠ በማስመሰል ክፍያ መፈፀም፣ ሌሎች የወጪ ሰነዶችን በማዘጋጀት ክፍያ መፈፀም፣ከተለያየ ሂሳብ ላይ በተመሳሳይ ቀናት ውሎ አበል መክፈል፤ በስልጠና ያልተሳተፉ ሰዎች ስምን አካቶ መክፈል፤ከቦታው ታሪፍ በላይ እና በመደበኛ ስራ ላይ እያሉ ውሎ አበል መከፈል፤ የመስተንግዶ ወጪዎችን አስቀድሞ በውድድር የተመረጠ አቅራቢ አለመለየት፤የተሳታፊዎችን ማንነትና የሚገባቸውን መስተንግዶ ዓይነትና መጠን በግልጽና ይህንኑ በሚያሳይ ውሳኔ አለማስደገፍ፤ ለብክነት በር በከፈተ አሰራር መፈፀም፣

- የግንባታ የስራ ስፍ ልኬት፣የስራ ዝርዝር እና የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸም፣ በሂሳብ ስሌት ስህተት ክፍያ መፈፀም፣ቀደም ባሉ ዙር ክፍያዎች የተሰራንና ክፍያ የተፈጸመበትን በድጋሚ መክፈል፤ለስራው ከተያዘው ውል በላይ ያለተጨማሪ ውል ክፍያ መፈጸም፤
- ተገቢውን ስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ ወደ ግዥ አለመግባትና የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ/ንብረት ገዝቶ ገቢ ማድረግ፤(ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቶ ከነበረም ከዚያ ውጭ መረከብ፤
- አስቀድሞ የተጠቃለለ የግዥ እቅድ አለማዘጋጀት እና የግልጽ ጨረታ ዘዴን የመጀመሪያ ምርጫ አለማድረግ ብሎም የግዥ ዘዴዎችን በተጨባጭ ምክንያት ላይ ተመስርቶ አለመምረጥና የግዥ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት መዝግቦ/ቃለ ጉባዔ ይዞ ለ3ኛ ወገን በተጨባጭ ማስረጃነት አለማያያዝ፤
- ተገቢ ማስረጃ (የግዥ ጥያቄ፤ የጨረታ ማስታወቂያ፤የተወዳደሪዎች ሰነድ፤ፕሮፎርማ፤ ቃለ ጉባዔ ውሳኔ፤ለፕሮጄክት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ማረጋገጫ(Payment certificate) የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤ የውል ሰነዶችን ወዘተ . . የመሳሰሉት) ተሟልተውና ተያይዞ ሳይቀርቡ ክፍያ መፈፀም፤
- ወጭ የተፈፀመባቸውን የወጭ ማስረጃዎች ለኦዲት ያለማቅረብ፣
- ላልተሰራ ስራ ሃሰተኛ የወጭ ማስረጃዎች በማዘጋጀት ክፍያ መፈፀም ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ምዕራፍ -5:- ማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶች፤

4.1 የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!

ማጠቃለያ፣

1. በዚህ አጭር ሪፖርት በዝርዝር እንደተመለከተው በ2014 በጀት ዓመት ሂሳቦች ላይ በተደረገው ኦዲት የጥሬ ገንዘብና የንብረት ሂሳብ ጉድለት፣የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ገቢ፣ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት ወጭ፣ አላግባብ የተከፈለ ክፍያ የጨመረ ሲሆን ስርዓቱን ባልተከተለ መንገድ የተፈፀመ የግንባታ ክፍያ፣ የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ ግዥ፣ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጭ እና ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ማስረጃ የግኝቱ ሁኔታ የቀነሰ መሆኑን መረጃው ያሳያል።

   በጥቅሉ ከ2010 እስከ 2014 ያሉት 5 በጀት ዓመታት ሂደቱ ሲገመገም የአብዛኛው ሂሳቦች ግኝት እየተሻሻለ አለመምጣቱን ያመላክታል።

የጥሬ ገንዘብ እና የንብረት ሂሳብ በሚመለከት፤

- የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ በ13 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 5,647,536.63 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከቀድሞው ገንዘብ ያዦች ብር 5,625,962.10 በጉድለት ተገኝቷል።

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ4 መ/ቤት ብር 1,064,146.79 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ (ጥሬ ገንዘብ በማነስ) እና በ1 መ/ቤት ብር 2,596,842.49 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሌጀር ከወጭ ቀሪ በመብለጥ ተስተውሏል።

- በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 271 መ/ቤቶች መካከል በ104 መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል።
- የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ በ0 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 10,623,805.32 በጉድለት ተገኝቷል።

የገቢ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በ3 መ/ቤቶች ብር 15,526,533.70 የማጭበርበር ድርጊት ተፈጽሞ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- በ1 መ/ቤት ብር 2,398,051.18 የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይሰበሰብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፣
- የ**2014** በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ**68** መ/ቤቶች ብር 412,805,098.78 ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፣

- ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሚልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ48 መ/ቤቶች ብር 916,031,374.02 የያዙ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፣
- በ12 መ/ቤቶች ብር 194,243.63 ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ስራ ግብር ሳይሰበሰብ ተገኝተቷል፣

የተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት፤

- የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ140 መ/ቤቶች ብር 4,248,867,738.87 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡
- የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ33 መ/ቤቶች ብር **1,829,855,394.64** የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፤

- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ8 መ/ቤቶች ብር 16,426.976.22 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 914,047.87 ለሚመለከተው ፈሰስ ሳደረግ የተገኘ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ109 መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ፣አላግባብ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 10,406,426.44 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉ፣በሥራ ዝርዝሩ እና በስራ ስፍር ልኬት መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ23 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 14,842,625.51 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፣
- ማንኛውም ክፍያ በወጭ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ ሲገባው ይህን በመተላለፍ በ20 መ/ቤቶች የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር 7,939,701.65 የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞና ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሚልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ9 መ/ቤቶች ብር 29,148,709.87 ስለ ክፍያው ትክክለኛነት የሚያስረዳ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- የዕቃዎች አገልግሎቶች የግዥ ስርዓቱን ያልጠበቀ በ55 መ/ቤቶች ብር 46,599,847.46 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ስርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት፤

- የ2014 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ118 መ/ቤቶች ብር 1,134,090,400.78 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይከፈል ወይም ወደ ተጣራ ሀብት ሳይቀየር ተገኝቷል፡፡
- የ2014 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ35 መ/ቤቶች ብር 375,126,301.53 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ አስተያየት፤

በ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶችን እናቀርባለን፣

በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ፤

በኦዲት ስራው ከተስተዋሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአንዳንድ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተከሰተ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ እየተዳረገ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡ እና የተዘረጋውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

የገቢ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን የአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

በገቢ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ መሰብሰብ እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን የአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤

በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ማጠናከር ስለማስፈለጉ

በኦዲት ውጤቱ መሰረት መረዳት እንደተቻለው በበርካታ መ/ቤቶች ተሰብሳቢ ሂሳቡ መቸ እንደተሰጠ፣ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ ምንጩን የሚያሳውቅ የተሰብሳቢ ሂሣብ

ተቀጽላ ሌጀር እየተዘጋጀ ባለመሆኑ ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት ይገባል፡፡

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ የሚገባ ሲሆን ይህን ተግባራዊ በማያደርጉ የየተቋሙ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ስራን ባልተመቸ ሁኔታ መምራትና ለብክነት በር በመክፈት ድርጊት ሊጠየቁ ይገባል፡፡

የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና ማሻሻያ አስተያየቶች ትግበራ ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፣ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ላይ በየደረጃው በሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የፍትህ አካላት አማካኝነት ክትትል ሊደረግበት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ኮሚቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡

በየደረጃው ያሉ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጭ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀርብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡

አመስግናለሁ!!

አማረ ብርሀኑ /ዶ/ር /

ዋና ኦዲተር

ሰኔ/2015